ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-
ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ

( በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አዲሱ መሰለ

ነሐሴ 2016

ጅማ ኢትዮጵያ

# ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ

( በአስረኛ  ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን ለማስተማር(TeAm)

ለማስተርስ ዲግሪ ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በ

አዲሱ መሰለ

አማካሪ

ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

ነሐሴ 2016

ጅማ ኢትዮጵያ

# በጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

# ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

‹‹ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ በአስረኛ  ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት››በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ አማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ሚሚያነት በአዲሱ መሰለ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ---------------------------------------- ፊርማ------------------- ቀን-------------------

የውስጥ ፈታኝ------------------------------- ፊርማ------------------- ቀን--------------------

የውጭ ፈታኝ--------------------------------- ፊርማ----------------- ቀን-------------------

## የጥናቱ ማረጋገጫ

‹‹ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ በአስረኛ  ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ማስተማር ሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን የተጠቀምኩባቸው ድርሳናት በትክክል ዋቢ መሆናቸውንና ጅማ ዩኒቨርሲቲም ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም-------------------------------------------------

ፊርማ---------------------------------------------

ቀን-------------------------------------------------

ማውጫ

ይዘት ገጽ


ማውጫ-----------------------------------------------------------------------------------------------------------i

ማውጫ…………………………………………………………………………………………….iv

ምስጋና……………………………………………………………………………………………..v

አጠቃሎ……………………………………………………………………………………………vi

ምእራፍ አንድ ........................................................................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ .......................................................................................................................... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት----------------------------------------------------------------------- ------- 3

1.3. የጥናቱ መላምት .................................................................................................................. 5

1.4. የጥናቱ አላማ....................................................................................................................... 5

1.4.1. አብይ አላማ ................................................................................................................... 5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ.................................................................................................................. 5

1.6. የጥናቱ ወሰን........................................................................................................................ 6

1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ፍቺ.................................................................................................. 7

ምዕራፍ ሁለት .......................................................................................................................... 8

2.1 ክለሳ ድርሳናት.................................................................................................................... 8

2.1 ከጽህፈት ትምህርት ጋር የተያያዙ የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሳብ……………………………… 8

2.2.1 የጽሁፋዊ ንጽጽሮሽ ንድፈ ሃሳብ...................................................................................... 8

2.2.2 የግንዛቤ እድገት ንድፈ ሀሳብ............................................................................................ 9

2.2.3 የተግባቦታዊ ንድፈ ሀሳብ ( Communiction Theory ).............................................. 10

2.2.4 የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (social construction Theory)................................. 10

2.1. 1 የመጻፍ ክሂል................................................................................................................... 11

2.1.2 የመጻፍ ክሂል ምንነት ....................................................................................................... 13

2.1.3 የመጻፍ ትምህርት አላማ ................................................................................................. 14

2.1.4 በጽህፈት ትምህርት ሂደት የሚፈጠሩቸችግሮች .......................................................... 15

2.1.4 በመጻፍ ትምህርት ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች.................................................................. 16

2.1.5 የመጻፍ ክሂል አስፈላጊነት .............................................................................................. 16

2.1.5.1 ውጤት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ........ 18
2.1.5.3 ኢ.ርቱእ (indirect) የጽህፈት ምዘና ........ 24
2.1.5.4 ርቱእ (direct) የጽህፈት ምዘና ........ 25
2.2.ጥናቱ የሚከተለው ጽንሰ ሀሳባዊ ማእቀፍ ........ 26
2.6 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 27
ምዕራፍ ሶስት........ 29
የጥናቱ ዘዴ ........ 29
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 29
3.2. የናሙናዎች አመራረጥ ዘዴ ........ 29
3.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ ........ 30
3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ ........ 30
3.2.4 የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ ........ 31
ይህ ጥናት ተዛምዷዊ ጥናት ሲሆን ዋና ትኩረቱም........ 31
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 32
3.3.1. ፈተና ........ 32
3.3.2. ቅድመ ትምህርት ፈተና ........ 32
3.3.3. ድህረ ትምህርት ፈተና ........ 33
3.3. 4 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 33
3.4. የመረጃ አደረጃጀት እና አተናተን ዘዴ........ 34
ምዕራፍ አራት........ 35
የጥናቱ መረጃ ትንተናና ማብራሪያ........ 35
4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና ........ 35
4.2.የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 45
ምእራፍ አምስት........ 48
5.1ማጠቃለያ ........ 48
5.2 መደምደሚያ ........ 50
5.3 አስያተያየት ........ 50

ዋቢ ጽሑፎች……………………………………………………………………………………..52

አባሪ-1……………………………………………………………………………………………..56

በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠየቅ…………………………………………………..58

## ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ሰንጠረዥ 4.1፡- የተተኳሪ ቡድኖች ቅድመ ፈተና ውጤት ንጽጽር /በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/……………………………………………………………………………………36

ሰንጠረዥ 4.2፡- የተተኳሪ ቡድኖች ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት ንጽጽር/ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/……………………………………………………………………………………37

ሰንጠረዥ 4.3፡- የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር…………………………………………………………38

ሰንጠረዥ 4.5 የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ የመጻፍ ችሎታ ንጽጽር(በባእድ ናሙና ቲ ቴስት)……………………………………………………………………………39

ሰንጠረዥ 4.4፡- የቁጥጥር ቡድኑ ቀድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር…………………………………………………………41

ሰንጠረዥ 4.6 የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረ ጽህፈት የመማር ፍላጎት ንጽጽር በባእድ ናሙና ቲ ቴስት--------------------------------------------------------------42

ሰንጠረዥ 4.7 የቡድኖቹ ቅድመ እና የድህረ ጽህፈትን የመማር ፍላጎት የጽሁፍ………..45

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ነገሮችን ሁሉ አሳክቶ ለዚህ ላበቃኝ ልዑል እግዚአብሄር ምስጋና ይግባው፡፡ጥናቱን ስጀምር የመረጥኩትን ርዕስ ከማስተካከል ጀምሮ የሞያ ፍቅራቸውንና የዕውቀት ፍለጋቸውን በማመልከት ፈጣን ግብረመልስ እየሰጡ ስራዬን ያለምንም መታከትና መሰልቸት በተደጋጋሚ በማየትና በማረም ዕውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውን ጉልበታውን ሳይሰስቱ የኀበጠውን እያቃኑ ጥናቱ አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ ለዚህ ላበቁኝ  አማካሪዬ ለዶክተር ጥበቡ ሽቴ እና ለረዳት አማካሪዬ ዶክተር ለማ ንጋቱ ልባዊ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነዉ፡፡

እንዲሁም ይህን ጥናት ሳካሄድ ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር ያደረጉልኝ የእንጊቢ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን፤የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና እንዲሁም በጥናቱ ተሳታፊዎች ለነበሩት የእንጊቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ”B” እና “F” ክፍል ተማሪዎች ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ላለፍኩበት የትምህርት ጊዜያት ሁሌም ከጎኔ ላልተለየችኝ እና የተለያየ ሀሳብ በመስጠት ለስራዬ መሳካት ሞያዊ እገዛ ላደረገችኝ ባለቤቴ መምህርት ምስራቹ አያና እና ለልጆቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋና አቀረወባለሁ፡፡

# አጠቃለሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ያለዉ አስተዋጽኦ መለየት ነው፡፡ ጥናቱም ከፊል ሙከራዊ ሲሆን ፤ የተካሄደዉም በኦሮሚያ ክልል በቡኖ በደሌ ዞን በበደሌ ከተማ በሚገኘው በእንጊቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና ስልት ከተመረጡ በኋላ ፤ በቀላል የእጣ ናሙና ስልት በአንድ መምህር ከሚማሩ ስድስት ምድብ ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ስልት ሁለት ምድቦች ከተለዩ በኋላ በተራ የእጣ ናሙና ስልት አንዱ የሙከራ ሌላኛዉ የቁጥጥር ቡድን ሆኖ በጥናቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፈተና ስራ ላይ ዉለዋል፡፡ ፈተናዉ ቅድመ እና ድህረ ፈተናን ያካተተ ነው፡፡ ቅድመ ፈተናዉ የተሰጠበት አላማ ተማሪዎች ከሙከራ ጥናቱ በፊት ያላቸዉን የመጻፍ ክሂል ውጤት ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመለየት ሲባል ነዉ፡፡ የድህረ ፈተናው አላማ ደግሞ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ሆነው የተመረጡት ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ክሂልን ከተማሩ በኋላ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት መኖር  አለመኖሩን ለመለየት ነው፡፡

ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች ከመጻፍ ልምምዱ በፊትና በኋላ ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች የተፈተኑትን ፈተና በባእድና በጥንድ ቲ-ቴስት ስሌት ተሰልቶ ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይቷል፡፡በጥናቱ ግኝት መሰረት ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የተማሩት የሙከራዉ ቡድን ተጠኚዎች ከቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት በ 8.0926 አማካይ ውጤት ብልጫ ማስመዝገባቸዉ፣ ብሎም በባእድና በጥንድ ናሙናዎች ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ዉጤቱ (t=-2.799, df=60, p=0.001) አረጋግጧል፡፡ በዚህ መሰረት ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂል ማስተማር በሰፊዉ ከተለመደው የመጻፍ ክሂልን ከማስተማር ዘዴ በመማሪያ መጽሐፍ በቀረቡ የመጻፍ ክሂል ተግባራት በተሻለ መልኩ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ውጤት ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያለዉ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ ይህም ውጤት ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ተጥቅሞ  የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሳደግ አኳያ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለዉ ሊጠቁም ችሏል፡፡

# ምእራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የመጻፍ ኪሂል በጣም ወሳኝ ሚና አለው፡፡በመሆኑም ክሂሉ ለተማሪዎች በጣም አስፈላጊ ነው:: Haerazi and Irawan,(2019) እንደገለጹት የመጻፍ ክሂልን መማር እንደ መናገር ክሂል በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚካኑት ክሂል ነው፡፡ስለሆነም ክሂሉን ሳይንሳዊ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ተገቢ ነው፡፡

የመጻፍ ክሂል ህግጋት ውስብስብ በመሆናቸው ለተማሪዎች አስቸጋሪ ናቸው፡፡በርካታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የመጻፍ ክሂልን መማር በጣም አስቸጋሪ ተግባር ነው፡፡Sajid and Siddiqui(2015) እንደሚያስረዱት ክሂሉ አስቸጋሪ የሆነው አንድን ጉዳይ በጽሁፍ ለመግለጽ የስነልሳን እውቀትንና የተግባቦት ብቃትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡

የጽህፈት ክሂል በትምህርት መሰጠት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ የጽህፈት ትምህርት አቀራረቦች አገልግሎት ላይ ዉለዋል፡፡ የመጀመሪያዉ ውጤት ተኮር አቀራረብ ሲሆን ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለይም በ1960 ዎቹ አከባቢ በስፋት ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ዋነኛ አላማዉም ተማሪዎች መዋቅር (የቋንቋ ህግጋት) ላይ ተመስርተዉ የመጻፍ ክሂል እንዲማሩ ማስቻል ነው፡፡ በዚህም አቀራረብ፤የትምህርት አላማ ከግብ መድረሱ የሚረጋገጠው ተማሪዎች የሚጽፉትን የመጨረሻ ድርሰት በጥልቀት በማየት ነው፡፡

(Nunan, 1989,1991)፡፡ ይህ አቀራረብ ለቅርጽ ትኩረት መስጠቱ ፤ተማሪዎቹ በራሳቸዉ ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ተግባራትን እየፈጠሩ እንዲለማመዱ የማድረግ ሁነታ ዝቅተኛ መሆኑ፤ እንዲሁም የትምህርቱ ሂደት መምህር መራሽ አቀራረብ ላይ መመስረቱ በዋነኛነት በደካማ ጎን የሚነሱ ነጥቦች ናቸዉ፡፡ ዉጤታማ የመጻፍ አቀራረብ ትምህረት ውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉ አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ በመረዳት ነው፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን ሂደት ተኮር የማስተማርያ ዘዴ በቀጣይነት ሊመጣ ችሏል፡፡የዚህ አቀራረብ ዋነኛ ትኩረት ምን ተፃፈ በሚለው የመጨረሻ ዉጤት ሳይሆን፣ እንዴት ተፃፈ በሚለዉ ሂደት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በስተመጨረሻ ከሚያዘጋጁት ጽሁፍ ይልቅ ጽሁፉን ለማቀነባበር ለሚጠቀሟቸው ልዩ ልዩ ሂደታዊ ተግባራት ትልቅ ዋጋ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ጽሁፉን ለማቀነባበር የሚያልፏቸዉ ሂደቶች ለውጤታቸው ማማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ

ይታሰባል፡፡ በትምህርቱ ሂደት የመምህሩ የበላይነት እና ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ተማሪዎች በራሳቸው የጽህፈትን ፍጥነት እየተለማመዱ የመጻፍ ስራቸውን ያከናዉናሉ እንጂ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት እንዲያስቡ (እንዲያጤኑ) የሚያደርግ አይደለም (RAIMES 1983 NUNAN1989 RICHARDS 1990 እና HYILAND 2003) ፡፡ ይህም አቀራረብ ምንም እንኳን  መጻፍ ሂደታዊ ቢሆንም ተማሪዎች በስተመጨረሻ በሚጽፉት ድርሰት ላይ ትኩረት አለመሰጠቱ እና በሰዋሰዋዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አለመደረጉ ትችት እንዲነሳበት ምክንያት ሆኗል፡፡

ከሂደታዊ የመጻፍ ትምህረት አቀራረብ ላይ የመጣው ዘውግ ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን አቀራረቡ ለሰዋሰዋዊ ህግጋት ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡ ህግጋቱ ግን ከማህበረሰቡ አዉድ ጋር ተዋህደዉ መቅረብ እንደሚኖርባቸዉ የሚያምን ነው፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ዘርፎች ላይ መሰረት መደረጉ ይዘቶችን በማምጣት ተማሪዎች የቋንቋ መዋቅሩን፣ የማህበረሰቡን ተግባቦት ባገናዘበ መልኩ የትምህርቱን ሂደት እንዲያከናዉኑ ማስቻል ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው፡፡

(RAIMES 1983 NUNAN1983 RICHARDS 1990 እና  HYLAND 2003) በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን የተለያዩ ታሪኮችን ፍቺ ለመስጠት ጥረት ቢያደርጉም በራሳቸው እየፈጠሩ እንዲማሩ የማድረጉ ሁኔታ አነስተኛ ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም እንዴት መጠቀም እንዳለባቸዉ በመምህሩ የሚሰጠው ገለፃ ሰፊ መሆኑ የዘዉግ ተኮር አቀራረብ ትችት እንዲነሳበት ምክንያት ሆኗል፡፡
በአጠቃላይ ሶስቱም የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ቢኖራቸዉም የሚነሱባቸዉ ትችቶች እዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የተሻለ የመፃፍ ትምህርት አዉድን ለመፍጠር የሚችል መጻፍን ማስተማር ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሙከራዊ በሆነ ጥናት እየፈተሹ ውጤታማነታቸውን ማረጋግጥነው፡፡ ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪይ ዘዴ ለቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴነት በስፋት ጥቅም ላይ ሲውል የነበረ ነው፡፡ ስለሆነም የረዥም ጊዜ ታሪክ አለው፡፡ይህ የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ አቀራረብ ተማሪዎች መምህራኖቻችው አስቀድመዉ ባለማመዱቸዉ ወይም በሰጧቸዉ ጽሁፍ መሰረት በስተመጨረሻ የየራሳቸዉን የጽሁፍ ውጤት እንዲያቅርቡ የሚያበረታታ ነው፡፡ የስነ ዘዴው ዋነኛ አላማ ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ስነ-ላሳናዊ እዉቀት በማቅረብ ያንን በጽሁፍ ስራዎቻቸው ውስጥ እንዲጠቀሙበት ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ተመሪዎች አስቀድመው ስለ ቋንቋው ማወቅ አለባቸዉ (ሰዋሰዉን) የሚል እንድምታ አለው፡፡ ተማሪዎች ወደ ጽህፈት ተግባሩ ሲገቡ የተማሯቸዉን የሚመስሉ ቀለል ያሉ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ከሚጽፉት ጉዳይ ጋር የነበራቸዉን ትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀም በተግባር ላይ ለማዋል የቀረቡላቸዉን ሞዴል ጽሑፍ

በመቅዳት (በመኮረጅ) እና በመጨረሻም በአዲሱ ሥራቸዉ (አንቀጽ ወይም ድርሰት) ውስጥ እንዲያንጸባርቁ ያደርጋል፡፡

ይህንን ካደረጉ በኋላ የጽሁፍ ሥራቸዉን እንዲገመግሙ ሳይሆን እንዲታረሙና ውጤት እንዲሰጥባቸው ለመምህራኖቻቸው ያቀርባሉ፡፡ በአንጻሩ ግን መምህሩ ተማሪዎቹ በስራዎቻቸዉ ላይ አስፈላጊውን ማስተካከያ አድረገው በድጋሚ እንዲያቀርቧቸው ሊጠይቋቸዉ ይችላሉ (ምንም እንኳን ዉጤቱ አስቀድሞ የተሰጣቸዉ ቢሆንም )፤ በጣም የተለመደው፡፡

በአጠቃላይ አንዳድን የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ለአንዳድ ተማሪዎች ምቹ ሊሆኑ ቢችሉም ሌሎቹ ደግሞ ምቹ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡እንዲሁም Fareed(2016) እና Nacira (2010) እንደሚገልጹት የሁለተኛ ቋነቋ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መንስኤዎች ብለው ከዘረዘሯቻ የማስተማሪያ ዘዴ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ይገኙበታል፡፡ይህም ሁሉንም ተማሪዎች ያማከሉ ዘዴዎች አስፈላጊ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡በዚህ ጥናትም አንዱ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ የሆነው ውጤት ተኮር የጽህፈት ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ከተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል ተመርምሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጽህፈት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሲሆን የሰው ልጅ ሀሳቡንና ስሜቱን ለመግለጽ ፣ መልእክት ለማስተላለፍ ፣ በአለም ላይ የሚፈጸሙ ሁነቶችን በተመለከተ መረጃ ለመለዋወጥ ፣ ስለራሱም ሆነ ስለሌሎች በጥልቀት ለመረዳት፣ ባህልን፣ ወግንና ታሪክን በሰነድነት በማስቀመጥ ለመጭው ትውልድ ለማቆየት የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ Heawan (2005) ፣ Miller (1999) ፣ Hedge (1998) እና Riamis (1983) በመጥቀስ ገልጽዋል፡፡

ይሁን እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ክሂል ትምህርት ትኩረት እንዳነስውና በዚህም ረገድ የተማሪዎች የጽህፈት ችሎታ ደካማ እንደሆነ (ማረው ፣ 2005 ፣ አምሳሉና ደምሴ ፣ 1982 ፣ አለማየሁ ፣ 1986 ፣ ደረጀና ግርማ ፣ 1999) ገልጸዋል፡፡

የጽህፈት ክሂል ማስተማር በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ልምድ ቢኖርም እስካሁን የታለመለትን ግብ በሚጠበቀው መጠን ተሳክቶ አይታይም፡፡ ለዚህም ችግር ዋና ዋና የሚባሉት መምህራን የሚከተሉት የማስተማር ስልት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣ የክፍለ ጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ናቸው (ተስፋዬ፣1981)፡፡

የተለያዩ አጥኚዎች የጽህፈት ክሂል ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ጥናቶች አከናውነዋል፡፡ የጥናቶቹ አቅጣጫዎችም የተለያዩ ሲሆኑ የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል አለመዳበር ምክንያቶችን መመርመር ላይ ትኩረታቸውን ካደረጉ ጥናቶች መካከል መሰረት (2003 ) ተገኘ (2000)እና ሞገስ (2013) ጥናቶች ይገኙበታል፡፡ከዚህ ጥናት የተገኘው ጥናቶች የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክው በተማሪዎች ላይ የሚስተዋለው የመጻፍ ኪሂል አለመዳበር በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረ ሲሆን ከምክንያታቸው ውስጥ መምህራን የሚጠቀሙባቸው የማስተማሪያዘ ዴዎች ይገኙበታል፡፡ ተማሪዎች የመማር ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆን በቋንቋ ትምህርት ሂደቱ አሉታወዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ይታወቃል፡፡በመሆኑም ተደጋጋሚ ጥናቶችን በማከናወን ችግሮችነ መፍታት ለትምህርቱ ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ይህንን ሀሳብ ጥናት ያደረጉት ሰዎችና ምሁራን ይስማሙበታል፡፡(ሞገስ፣2013፤ባዬ 2003፤አንለይ፣2000)፡፡የመምህራንን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የገመገሙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኞቹ የአማርኛ ቋነቋ መምህራን የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ተገቢዎቹንየማስተማሪያ ዘዴዎች አይጠቀሙም (ሀና፣2003፤ተመስገን ፣2001፣አለማየሁ፣1998)፡፡

ከእነዚህ ጥናቶች የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው አፈ-ፈት ባልሆኑ ተማሪዎች ላይ የሚስተዋለው የመጻፍ ክሂል አለመዳበር በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረ ሲሆን ከምክንያቶቹ ውስጥም መምህራን የሚጠቀሙባቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች ይገኙበታል፡፡የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ዝቅተኛ መሆን በቋንቋ ትምህርት ሂደቱ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይታወቃል፡፡በመሆኑም ተደጋጋሚ ጥናቶችን በማከናወን ችግሩን መፍታት ለትምህርቱ ውጤታማነት ጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ አጥኚው በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ልምድ መታዘብ እንደቻለው አብዛኛዎቹ ያስተማራቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

አጥኚው ይህንን ጥናት ለማካሂድ የፈለገበት ዋናው ምክንያት መደበኛ ስራውን በሚሰራበት በቡኖ በደሌ ዞን በበደሌ ከተማ በእንጊቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂላቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት ተኮር ማስተምሪያ ዘዴ መጠቀም የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ ለመለየት በማሰብ እና ተማሪዎች የሚጽፏቸው ድርሰቶች ከይዘት አደረጃጀት ፤ከቃላት፤ከቋንቋ አጠቃቀም እና ከስርዓት አጻጻፍ አንጻር ችግሮች እነደሚታይባቸው ያስተውል ነበር ፡፡ ስለዚህ ይህን ጥናት ውጤት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ በመጠቀም የጽህፈት ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ በሚል ርእስ ከፊል ሙከራዊ

ጥናት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ለማካሄድ አጥኚው ተጠቅሞ ማስተማር በመፈለጉ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስቷል ፡፡

## 1.3. የጥናቱ መላምት

ጥናቱ የሚከተሉትን መላምቶችን አስቀምጧል፡፡

- ዉጤት ተኮር የጽህፈትን የማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ አለው፡፡
- ዉጤት ተኮር የጽህፈትን የማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ የለውም፡፡

## 1.4. የጥናቱ አላማ

### 1.4.1. አብይ አላማ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ የጽህፈት ችሎታ እድገት በዉጤት ተኮር ጽህፈትን ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚኖረውን አስተዋጽኦ መመርመር ነው።

#### *1.4.1.1 ዝርዝር አላማ*

- ተማሪው ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍን ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ፡፡
- ተማሪው ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ መማሩ ያስገኘለትን አስተዋጽኦ መለየት፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

በዚህ ጥናት የሚገኝ ውጤት አውንታዊ ከሆነ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል:: መምህራን ውጤት ተኮር የጽህፈትን የማስተማሪ ዘዴን ተጠቅመው የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉን አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ የሚያመለክት ውጤት ያስገኛል ፡፡እንዲሁም ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ዉጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉን አስተዋጽዖ እንደ ማሳያነት ያገለግላል፡፡በተጨማሪም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት መከናወኑ ለአጥኚዎች አስፈላጊያቸው ነው፡፡ ወደፊት በሚየደርጉት የመጻፍ ክሂል ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናቶች ከዚህ ጥናት የሚገኘውን ውጤት በመነሻ ሀሳብነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤በጥናት ሂደታቸውም በርዕሱ ዙሪያ ጥናት ለሚያጠኑ ሰዎች እንደ ማጣቀሻነት ያገለግላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከርእሰ ጉዳዩ፣ ከማጥኛ ስፍራ እና ከተጠኚዎች አንጻር የራሱ ወሰኖች አሉት፡፡ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይዮች አንጻር ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉ አስተዋጽኦ ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡ከማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥም ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ የማስተማሪያ ዘዴዎች በጥናቱ አይካተቱም፡፡እንዲሁም ከመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች ውስጥ ይህ ጥናት በጽሁፉ ይዘት ፣በጽሁፍ አደረጃጀት፣በቋንቋ አጠቃቀም፣በቃላት ምርጫ እና ንዑሳን ክሂሎች በዚህ ጥናት አይካትቱም፡፡

ከማጥኛው ስፍራና ከተጠኚ ተማሪዎች አንጻር ጥናቱ የሚያተኩረው ጥናቱ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል፣ በቡኖ በደሌ ዞን በበደሌ ከተማ በ2016 የትምህርት ዘመን በእንጊቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማርኛ ቋንቋን ትምህርት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነዉ፡፡ ሌሎችን የክፍል ደረጃዎች አይመለከትም ምክንያቱም ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ በመሆኑ አጥኚዉ መደበኛ ስራውን በሚሰራበት ቦታ የጥናቱን ተሳታፊዎች በቅርበት ለማግኘትና ለማከናወን ስለሚያስችል ተመራጭ አድርጎታል፡፡ ማሬ (2008) ፤ Gham and perin (2007)ን ጠቅሶ እንደገለጸዉ የመፃፍ ትምህርትን አስመልክቶ የሚደረጉ ጥናቶች በመካከለኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ በርካታ ስራዎች ቢሰሩ ተማሪዎቹ እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ ችሎታቸዉን እያሻሻሉ ይሄዳሉ የሚል አስተያየት በመኖሩ ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የሚካሄደዉ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ነዉ፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ፍቺ

የጽህፈት ክሂል፡- የቋንዉን ስርዓት በጠበቀ መልኩ ሀሣብን ወይም ስሜትን በጽሁፍ መግለጽ ማለት ነዉ፡፡

ውጤት ተኮር፡- የማስተማሪያ ዘዴ፡-በእዉቀት እና በክህሎት ላይ ያተኮረ ትምህርት ተማሪዎችን በእዉቀት ወይም በክህሎት ትክክለኛነት መገምገም ማለት ነዉ፡፡

ቅድመ ምዘና፡- መደበኛ (ቅድመ ሙከራ ፈተና) የተማሪውን ዝግጁነት ለመፈተሽ የሚቀርብ ግምገማ ነው፡፡

የቁጥጥር ቡድን፡- በተለመደው የትምህርት አሰጣጥ እና አደረጃጀት እንዲሳተፍ የሚደረግ ቡድን ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምእራፍ ስርከ የዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ተዳሰዋል፡፡በዋነነኛነትም የጽህፈት ክሂል ንድፈ ሀሳቦች እና ምንነት፣በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የውጤት ምንነትእና አይነቶች፣የውጤት ተኮር የቋንቋ ማስተማር አቀራረብ ምንነት፤በጽህፈት ትምህርት ሂደት የውጤት ተኮር የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የውጤት ተኮር የቋንቋ ማስተማር ሞዴሎች በዝርዝር ከቀረቡ ቦኋላ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላችው የቀደምት ስራዎች እንዲቃኙ ተደርገዋል፡፡

## 2.1 ከጽህፈት ትምህርት ጋር የተያያዙ የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሳብ

የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሳቦች ላይ ተመስርተው በመጻፍ ክሂል ላይ ጥናት የተካሄደባቸው እና ወደፊት ጥናት ሊካሄድባቸው የሚችሉ የተለያዩ የጽህፈት ኪሂል ንድፈ ሀሳቦች አሉ፡፡ እነዚህም ንድፈ ሃሳቦች በዋናኛነት በአራት የሚከፈሉ ሲሆን:- እነሱም ጽሁፋዊ ንጽጽሮሽ ንድፈ ሃሳብ፣ግንዛቤአዊ- ዕድገት፣ንድፈ ሃሳባዊ ተግባቦት እና የማህበረ ግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ ናችው፡፡እንዳንዱን ንድፈ ሃሳብ ውስጥ የሚነሱ የትኩረት አቅጣጫዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡

### 2.2.1 የጽሁፋዊ ንጽጽሮሽ ንድፈ ሃሳብ

የጽሁፍ ንጽጽሮሽ ንድፈ ሃሳብ የተዋወቀው በkaplan(1966) ሲሆን ዋነኛ መነሻው ያደረገውም አፈ-ፈት እና አፈ-ፈት ባልሆኑ ተናጋሪዎች መካከል የሚጻፉ ጽሁፎችን በማነጻጸር ነው፡፡በ1960ዎቹ አዳምጦ መናገር ዘዴ ተግባር ላይ የዋለበት ጊዜ በመሆኑ፤ከማዳመጥ እና ከመናገር ውጪ ትኩረት የተሰጠው ክሂል አልነበርም ማለት ይቻላል፡፡ይህን ተከተትሎ Kaplan ለመጻፍ ክሂል ትኩረት መሰጠት እነዳለበት በማስብ ይህንነ ንድፈ ሀሳብ በጊዜው ሊቀመሩ ችለዋል፡፡ በዚህም ጊዜ Kaplan ከአውሮፓና ከኢሺያ ሀገራት የተውጣጡ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች በጥናታቸው ካካተቱ በኋላ ንጽጽራዊ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ያገኙት ዋነኛው መሰረታዊ ነጥብ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቻይንኛ፣ አረብኛ እና አይርሽ፣ ጃፓንኛ እና ፈረንሳይኛ የሆኑ ተማሪዎች የጻፏቸው ድርሰቶች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከሚጽፏቸው ጽሁፎች የተለያዩ እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞም

በእያንዳንዱ ቋንቋ እና ባህል ውስጥ የተለያየ የአንቀጽ ቅደም ተከተል እንዳለ በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡

የጽሁፍ ንጽጽሮሽ ንድፈ ሀሳብ ብዙ ትችቶችን አስተናግዷል፡፡ ሆኖም ግን የጽህፈት ክሂልን በማስተማር ሂደት ውስጥ ንድፈ ሀሳቡ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ይናገራሉ፡፡ይህንን በማስመልከት siliva(1990) እንደገለጹት የአንቀጽ አላባውያን የሚባሉት ሀይለቃል፣ ዝርዝር ዐረፍተ ነገሮች እና መሸጋገሪያ ቃላት እንዲሁም ዛሬ ላይ በአንቀጽ ማስፋፍያ ውስጥ የሚጠቀሱ ብያኔ ማወዳደር ፣ ማነጻጸር፣ የማዋገን ስልቶች ወዘተ.... የዚህ ንድፈ ሀሳብ ዋናዋና ትሩፋቶች ናቸው፡፡ እንደ ሀሳቡ ለሰላሳ አመታት ተግባር ላይ ሲውል connor (2002) ዋነኛ የንድፈ ሀሳቡ የትኩረት አቅጫዎች በአራት ከፍለውታል፡፡

የመጀመሪያው የጽሁፍ ዲስኩር ትንታኔን ዘዴን በመጠቀም አንዳንድ ጽሁፍ በተለያዩ ቋንቋዎች እና ባህሎች እንዴት እንደሚተረጎም ማወዳደር እና ማነጻጸር መቻል ነው፡፡ ሁለተኛው የትኩረት ነጥብ የመጀመርያ ቋንቋ እና ባህል በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ውስጥ ያለውን ተጽኖ መፈተሽ ነው፡፡ ሶስተኛው መማርያ ክፍል ላይ የተመሰረተ ንጽጽሮሽ ነው፡፡ ይኸውም በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የራሳቸውን ባህል ከሌላኛው ተማሪ ባህል ጋር እያነጻጸሩ የመደገፍ ተግባር በበማሳየት የተሰጣቸውን ተግባር እንዲያከናውኑ መርዳት ነው፡፡ አራተኛው ዘውግ ውስን ፍተሻ (Genere specific Inverstigation) ማካሄድ ነው፡፡ የጽሁፋዊ ንጽጽር ንድፈ ሀሳብ ለበርካታ ዓመታት ሲሰራበት ቢቆይም በዋናነት ሁለት መሰረታዊ ትችቶች ተነስተውበታል፡፡ የመጀመርያው ጽህፈት በውጤት ተኮር ላይ ብቻ ማተኮር እና ሂደቱን መዘንጋቱ ሲሆን ሌላኛው ትችት ደግሞ ንድፈ ሀሳቡ ትኩረት ያደረገው በቴክስት ላይ እንጂ በአእምሯዊ ሂደታዊ ክንውኖች አለመሆኑ ነው ፡፡( William and Kaplan 1996 ) በዚህም የተነሳ ሌሎች ንድፈ ሀሳቦችን ተከትለው እነደሚመጡ ምክንያት ሆኗል፡፡

### 2.2.2 የግንዛቤ እድገት ንድፈ ሀሳብ

ይህ ንድፈ ሀሳብ ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ድርሰቶች (አንቀጾች) ላይ ግንዛቤ ተጽእኖ እነዳለው ንድፈ ሀሳቡ ይገልጻል፡፡ በእንግሊዘኛ የመጻፍ አውድ ውስጥ በመነሳት Flower and hayese (1981) እና Bereister and scardamalia (1987) ያካሄዳቸው ጥናቶች ግንዛቤያዊ እድገት ንድፈ ሀሳብ እንዲጠናከር ምክንያት ሆኗል፡፡ በFlower and hayese (1981) ጥናት መጽሃፍ ማቀድ እና ማፍለቅን መተርጎምን እና አርትኦት ማካሄድን ተግባር እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በዚህ ሞዴል መሰረት የመጻፍ ተግባርነ ለማከናወን ተማሪዎቹ የሚጽፏቸው የመጻፍ ሂደቶች ተመሳሳይ ናቸው፡፡

ሆኖም ይህ ሞዴል በBereiter and scardamalid (1987) ትችት ተንጸባርቋል እንደ Bereiter and scardamalid (1987) አገላለጽ ሁሉም ጸሀፊዎች ተመሳሳይ ሂደት ሊያልፉ አይችሉም፡፡

በመሆኑም Flower and hayese (1981) ሞዴል ጥሩ እና የደካማ ጸሀፊዎች የሚጽፏቸው ሂደቶች ለየብቻቸው ተነጣጥለው አልተቀመጡም በማለት በሞዴሉ ላይ Bereiter and scardamalid (1987) ትችት ሊያነሱ ችለዋል፡፡

የተሰነዘረው ትችት መሰረት በማድረግ Bereiter and scardamalid (1987) ሁለት የመጻፍ ትምህርት ሞዴሎች አሳይቷል፡፡ የመጀመርያው እውቀትን የማሳወቅ ሞዴል (knowledge teling model) ተብሎ የሚጠራው ሲሆን ይህ ሞዴል የተዘጋጀው ለጀማሪ ጸሀፊዎች ነው፡፡ ሁለተኛው ሞዴል ደግሞ እውቀትን የማሸጋገር ሞዴል (knowledge transformation Model) ነው፡፡ ሞዴሉም የቀረበው ልምምድ ላለባቸው ጸሀፊዎች ነው፡፡ በውቀት የማሳየት ሞዴል አተያይ መሰረት ጀማሪ ጸሀፍት ውስብስብ መሆኑ ችግር ፈቺ የመጻፍ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ አይደረግም

## 2.2.3 የተግባቦታዊ ንድፈ ሀሳብ ( Communiction Theory )

ይህ ንድፈ ሀሳብ 1970ዎቹ አካባቢ የተመሰረተ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ንድፈ ሀሳቡ በዋነኛነት ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ተማሪዎች ተግባቦታዊ ችሎታ ላይ ነው፡፡ ለማንኛውም የመጻፍ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎቹ የሚያከናውኗቸው ተግባራት፤ተግባቦታዊ ሂደቶች ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው ንድፈሀሳቡ ይገልጻል፡፡ይህንን በተመለከተ Cooper and odell (1977) የተለያዩ ጽሁፋዊ የዲሰኩር አይነቶችን በዝርዝር ያሰቀመጡ ሲሆን እነሱም፡- ተውኔታዊ፣ ግለሰባዊ፣ ስነ ትምህርታዊ፣ ጽሁፎች፣ የንግድ ጽሁፎች፣ቴክኒካዊ ጽሁፎች፣ ልቦለዶች እና ግጥሞች ናቸው፡፡

## 2.2.4 የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (social construction Theory)

ይህ ንድፈ ሀሳብ በጽህፈት ትምህርት አውድ ውስጥ የላቀ ድርሻ አለው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ የሚያስተምር መምህር የጽህፈት ትምህርትን ከማህበራዊ እና ከዲስኩር አውዶች ጋር በማስተሳሰር የትምህረቱን ሂደት ሊያቀርብ ይገባል፡፡በማህበረ ግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ መምህሩ ሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ ብቻ ሳይሆን ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማር ዘዴ አቀራረብ ላይም በመመስረት የትምህርቱን ሂደት ሊያከናውን

ይገባል፡፡(zimmer man 1993) በውጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የጽህፈት ውጤቶች ላይ በመመስረት ትርጉም እየፈጠሩ እና እያደራጁ ይሄዳሉ፡፡በሂደታዊ አቀራረብ ደግሞ ተማሪዎች እርስ በእርስ እየተደጋገፉ እና ሃሳብ እየተለዋወጡ የጽህፈት ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡

ይህ ጥናት ጥኩረት ያደረገው በመጻፍ ኪሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችና የመጻፍ ችሎታ ላይ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህን ተለዋዋጮችን የተመለከቱ ጽንሰ ሃሳቦች አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ ምዕራፍ ከመጻፍ ክሂልና ከማስተማሪያ ዘዴዎቹ ጋር ተዛምዶ ያላችው ዘዴዎች ተቃኝተዋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የዚህ ምርምር ምንነት ለመገንዘብ እና ለመረዳት የሚያስችል የተለያዩ ድርሳናት ተከልሰዉ ቀርበዋል፡፡ በዚህም ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት፣ የተዛማች ጽሁፍ ቅኝት ማለትም የጽሁፍ ምንነት፣ የመጻፍ ትምህርት አስፈላጊነት፣ የመጻፍ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎቹ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች የዘርፉ ምሁራንን ሀሳብ በማጣቀስ ይቀርባሉ፤እንዲሁም ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ጥናቶችም ይቃኛሉ፡፡

## 2.1. 1 የመጻፍ ክሂል

የመጻፍ ክሂል በባህሪው ክሂለ ብዙ ነው፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአንቅጽ አመሰራርት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ለመጻፍ ክሂል ትምህርት ከሚያስፈልጉ ክሂሎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ ማረው (2003):: ክሂሉ እየጻፉ መማርን ይጠይቃል፡፡ ቢሆም ተማሪዎች በቀጥታ ወደ መጻፍ ስራ ከመግባታቸው በፊት በሂደቱ ላይ ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ለአብነት የሚከተሉትን ሂደቶች በቅደም ተከተል ማለፍ ይኖርባቸዋል::

ለምን እንደሚጽፉ በውል መገንዘብ፤ለማን እንደሚጽፉ ለይቶ ማወቅ፤በምልከታ፣ በማስታወሻ፣በመመዝገብ ፣እርስ በእርስ በማወያየትና በማንበብ አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ፤ እንዴት መጻፍና መረጃዎችን እንዴት ማደራጀት እንዳለባቸው የስራ እቅድ ማውጣት፤የመጀመርያ ረቂቅ መንደፍ፤ ረቂቁን መገምገም፣ መከለስ፣ በርካታ ረቂቆችን በተደጋጋሚ ካዘጋጁ በኋላ የመጨረሻውን ጽሁፍ መጻፍ፤ ለመጨረሻ ጊዜ እንደገና በጥልቀት አንብቦ መገምገም በአጠቃላይ የመጻፍ ኪሂልን ለመለማመድ ግራፎችን፣ ችግሮችና መፍትሄዎችን በጅምር የቀሩ አንቀጾችን፤ የአንቀጽ ቅደም ተከተላቸው የተዛባ ድርሰቶችን፣ የዐረፍተ ነገር ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አንቀጾችን ወዘተ መሰረት በማድረግ መስራት ይቻላል፡፡ ማረው(2003)፡፡ ጽሁፍ ተማሪዎች በተጨባጭ እውቀትና በአእምሮ ሂደት ውስጥ ሃሳብ፣ ፍላጎት፣ ልምድ፣ መልእክት፣ እና አመለካከታቸውን በቃላት የሚያስተላልፉበት የቋንቋ

ክሂል ነው ( Karimu፡2004) ፡፡የጽህፈት ክሂል እንደ ሁለተኛ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የበታች እንደሆነ ተደርጎ ይታያል (White: 1994):: ጽህፈት የሚጠቅመው በንግግር መልክ የተማሩትን ቋንቋ ለማጠናከር ነው (Byrne- 1991):: በአማርኛ ትምህርታቸው ውስጥ ከሚማሯቸው ይዘቶች አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው፡፡ ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ ክሂል እንዲያጎለብቱ ተገቢ የጽህፈት ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የጽሁፍ ትምህርት ለተማሪዎች በተገቢው መንገድ እንዲሰጥ ከተፈለገ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ የክፍል ውሰጥ የመማር ማስተማር ሂደት ዋናው አካል ድግሞ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ትምህርት የሚጠበቀውን ያህል ለውጥ እንዲያመጡ የትምህርቱ አቀራረብ እና ትምህርቱ የሚሰጥበት የማስተማሪያ ዘዴ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ ሚሰጠው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከግብ የሚደርሰው የትምህርቱ ይዘት ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማቅረብ ሲችል እንደሆነ ማሬ (2008) እነ Hawanm (2005), Vaner (1974) ን በመጥቀስ ገልጻለች፡፡

ጽህፈት በእይታዊ ትእምርቶች ውክልና በመገልገል ሰዎች ሃሳብ የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው፡፡ በመተላለፊያ ስልቱ ዕይታዊ፣ በአካላዊ ተግባቦታዊ አፍላቂ፣ በተግባቦታዊ ባህሪውም ርቱዕ ክሂል ነው (Widdowson፡1978፣ Harmer፡ 1991)፡፡

ጽህፈት ሃሳብን በትእምርት ወይም በቋንቋ የመወከል ሂደት ነው፡፡ ሂደቱም አካልንና አዕምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ በሀሪያቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወንና ከማሰብ ጋር የተቆራኘ ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው (Nunan፡ 1989)

እንዲሁም የጽፈት ችሎታን ለማሳደግ ለተማሪዎችን መነሻ የሚሆኑ ሞዴል ይቀርብላቸዋል፡፡ ከዝያም የቀረበላቸውን የጽሁፍ ሞዴል የቅርጽ፣ የይዘት እና የአደረጃጀት ባህርያት ለማጥናት ጽህፈትን ይተነትናሉ፤ በተጨማሪም ልሳናዊ ጉዳዮችን እና ቅንብራዊ አሰዳደሮችን ይለያሉ፡፡ የቀረበላቸውን ሞዴል ካጠኑና የቋንቋውን አላባውያን ከለዩ በኋላ ተመሳሳይ ጽሁፍ ለመጻፍ መነሻ የሚሆን አዲስ ግብአት ይሰጣቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በውጤት ተኮር ዘዴ አመለካከት የጽፈት ችሎታ በዐረፍተ ነገር ወይም በዲስኩር ደረጃ የተሰጡ ስደራዎችን ተከትሎ ትክክለኛ የቋንቋ ቅርጾችን የማዘጋጀት አቅም ተደርጎ ይታያል በለጠ (2006) ፡፡

ከዚህ እንደ ምንረዳው ጽህፈት በትምህርት የሚዳብር በተከታታይ ሙከራ የሚጎለብት የሰው ልጅ አእምሮዉንና አካሉን በማስተባበር ዕውቀቱን፣ገጠመኙን፣ ሀሳቡንና ውስጣዊ ስሜቱን በተገቢ ድምጻዊ ምልእክቶችን በመወከል ለመሰሎቹ የሚያስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡

## 2.1.2 የመጻፍ ክሂል ምንነት

መጻፍ የስሜት ህዋሳቶችን በማቀናጀት በርካታ ባህርያትን በአንድ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ውስብስብ የአዕምሮ ስራ ነው ( NUnan፡ 1998)፡፡ ጽህፈት አንድ ከቋንቋ አጠቃቀም ምሉዕ ከሚያደርጉበት ዋና ዋና ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በጽህፈት ክሂል የአንድን ቋንቋ ተጠቃሚ የሚፈልገውን መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ እንዲሁም መልዕክት ይቀበላል( Harmer፤ 1991)፡፡

ጽህፈት የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ትምህርቶችን በመጠቀም ሀሳብን በወረቀት ላይ የማስፈር ሂደት ነው፡፡ (Harmer 1991) ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂል ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠበቃል፡፡

የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የአንቀጽ አመሰራረት ለክሂሉ በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው (ማረው፤2010)፡፡

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት በሚሰጥባቸው አጠቃላይ አላማዎች ውስጥ አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ ሀሳቡን በጽሁፍ መግለጽ የሚችል እንዲሆን ማስቻል ነው (የአምላክ ስራ ፤2008)

በተጨማሪም ማረው (1996) ስለመጻፍ ምንነት በተመለከት እንደሚከተለው ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡

መጻፍ ክሂለ ብዙ ተግባር ነው፤ ርእስ የመምረጥና የማጥበብ ፤የቃላት አጠቃቀም፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ፣ የሀሳብ አፈላለግና አደረጃጀት የአንቀጽ አደረጃጀትና ብሎም ሙሉ ድርሰት የመጻፍ ችሎታዎችን ይጠይቃል፡፡ ክሂሉ እየጻፉ መማርን የሚጠይቅ በመሆኑ ወደ ጽሁፍ ስራ ከመግባቱ በፊት እና በኋላ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ የግድ ይላል፡፡

ከላይ የቀረበው ብያኔ እንደሚያመለክተው መጻፍ ሲታሰብ ተግባራትን ማከናወን እንደሚጠይቅ ነው፡፡ እነዚህም የሚከናወኑ ተግባራት ከርእስ መረጣ ጀምሮ እስከ ድርሰት መጻፍ ድረስ የሚዘልቁ ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ትምህርት ጠቀሜታ በተመለከተ የመስኩ ሙሁራን ሀሳባቸውን በተለያየ መንገድ ይገልጻሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Mercer and Mercer(1989) Hamil (1986)ን በመጥቀስ እንደሚገልጹት የመጻፍ ትምህርት በዋነኝነት ሶስት

ጠቀሜታዎችን ያስገኛል፡፡ የመጀመርያው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለመጻፍ ትምህርት ግንዛቤ አግኝተው ልዩ ልዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያስችላል፤ እንዲሁም ካገኙት ግንዛቤ በመነሳት መጻፍን ለሚጠይቁ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በሁለተኛነት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያገኙትን እውቀት መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጭ ሊያከናውኗቸው የሚችሏቸውን ተግባራት( ማመልከቻ መጻፍ፣ ቅጾችን መሙላት፣ ማስታወሻ መመያዝ …ወዘተ) ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲወጡ ያስችላል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ተማሪዎች የፈጠራ ጽሁፎችን ማለትም ግጥምች፣ ልቦለዶች፣ ታሪኮች…..ወዘተ መጻፍ እንዲችሉ አስተዋጽኦ ያደርግላቸዋል፡፡

### 2.1.3 የመጻፍ ትምህርት አላማ

ጽህፈት በትምህርት የሚሰጠው ለተለያዩ አላማዎች እንደሆነ ሙሁራኖች ያስረዳሉ፡፡ከእነዚህም ሙሁራን ውስጥ የተወሰኑትን በመጥቀስ በአላማነት ያስቀመጧቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡እንደ Raimse (1983) ገለጻ ተማሪዎች ጽህፈትን ሚማሩማቸው አላማዎች ዐረፍተ ነገርን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታይ የሚችል ነገር ነው፡፡ይኸውም ከአንባቢ ጋር ለመግባባት እንዲሁም በእለት ከእለት የህይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየት ሲባል የጽህፈት ትምህርት ይሰጣል፡፡ምሁሩም የጽህፈትን ትምህርት በማስተማር ሂደት ውስጥ ሊያተኩርባቸው የሚገባ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል ርቱዕነት እና ትክክለኘነትን ይጠቅሳሉ፡፡ርቱዕነት በሂደት ሊዳብር የሚችል የጽህፈት ትምህርት አንዱ አቅጣጫ ሲሆን ትክክለኘነት ደግሞ በታላሚው ቋንቋ መዋቅር (ሰዋሰው)ላይ ትኩረት ያደረገ የትምህርት ሌላኛው አቅጣጫ ነው፡፡ በመሆኑም በመጽሃፍ ትምህርት ሂደት በቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሂደት ላይ ትኩረት የሚደርግ ከሆነ ትክክለኛነትን ሲጠቅም ፣የጽህፈት ትምህርት በልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ትግባራት ተማሪዎቹ እንዲማሩ የማድረግ ተግባር ደግሞ ርቱዕነትን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Heaton(1991)የጽህፈት ትምህርት ኪሂልን አላማ ከንዑሳን ክሂል አላማዎች ጋር በማያያዝ ሐሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡ይኸውም የመጻፍ ክሂልን መማር የተለያዩ ጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን ተገቢነት ያላቸው ዐረፍተ ነገሮች መጻፍ፣ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ ላይ መጠቀም፣ተቀባይነት ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ ፣የዐረፍተ ነገሮችን አወቃቀር ስርዓትን ጠብቆ የመጻፍ እንዲሁም መደበኛ የሆነ የቋንቋ አተቃቀም የመለየት ተግባርን ይጠይቃል፡፡ከላይ ከቀረቡው ሙሁራን እይታዎች መረዳት አንደሚቻለው ጽህፈት ከአንባቢ ጋር ተግባቦት ለመፍጠር አዳዲስ ዕውቀቶችን ለማግኘት ፣አንድን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ በውስጡ ያለውን አመለካከት ለመግለጽ እና ለመደገፍ፣ልዩ ልዩ አእምሯዊ

ተግባራትን ለመወጣት እንዲሁም በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ሰዋሰዋዊ እና ተግባቦታዊ ክንውኖች ላይ ትኩረት ለማድረግ የሚካሄድ ጥረት እንደሆነ ነው፡፡

### 2.1.4 በጽህፈት ትምህርት ሂደት የሚፈጠሩቸችግሮች

ምሁራን ጽህፈት ብዙ ጥረት የሚጠይቅ አእምሯዊ ተግባር ተግባር እንደሆነ ይስማማሉ፡፡አእመሯዊ ጥረትን የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑም ተማሪዎች አንድ ጽሁፍ ለመጻፍ በሚሞክሩበት ሰዓት በርካታ ችግሮች ይገጥማቸዋል፡፡Byrne(1988) የጽህፈት ክሂሎች በተለያየ መልኩ አስቸጋሪ የሚያደርጉት ነጥቦችበሶስት ከፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ስነልቦናዊ ችግር ነው፡፡ለምሳሌ በንግግር ጊዜ አድማጭከጎን ይኖራል፤በጽህፈት ጊዜ ግን አንባቢ ከጎን የመኖሩ ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡በመሆኑም ጸሀፊው ቅጽበታዊ ምላሽእንደማገኝ በማወቅ ሀሳቡን በጽሁፍ ለመግለጽ ይሞክራል፡፡በዚህም የተነሳ ጸሀፊው ፣አንባቢውከጎን አንደሌለ በማሰብ ሀሳቡን በጽሁፍ ለመግልጽ ሲሞክር የመቸነቅ ስሜት እና ሌሎች ተያያዥ ስነ-ልቦናዊ ችግሮች ሊፈጥሩበት ይችላሉ፡፡ሁለተኛው ስነ ልቦናዊ ችግር ነው፡፡በንግግር ሂደት ለሰዋሰዋዊ ሁኔታዎች የመጨነቅ ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡ነገር ግን የጽህፈት ክሂል ለሰዋሰውም ሆነ ለተግባቦታዊ ሁኔታዎች ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ተጠንቅቆ መጻፍን ይጠይቃል፡፡

ሶስተኛው የግንዛቤ ችግር ነው፡፡ለአብነት ያህል ንግግር ተፈጥሯዊ በመሆኑ ለረጅም ሰዓት ሀሳብን በቀላሉ ለመግለጽ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ምንም እንኳ ግንዛቤ የራሱ ድርሻ ቢኖረውም መጻፍ ግን በዋነኝነት በመማር የሚገኝ ክሂል እንደመሆኑ መጠን በቂ ግንዛቤ ይጠይቃል፡፡ስለዚህ ጸሀፊው ግንዛቤ ከሌለው ሀሳቡን ለመግለጽ የሚቸገርበ ትሁኔታ ይፈጥራል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ Mohamed (2015)የተለያዩ ሙሁራንን በመጥቀስ እንደገለጹትተማሪዎች በመጻፍ ትምህርት ሂደት ከፊደል አጻጻፍ ስርዓት፣ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፤ከይዘት፤ከቃላት አመራረጥ፣ከዓረፍተ ነገር

አወቃቀር፣ከአንቀጽአደረጃጀት፣ወዘተ…አኳያ የሚከሰቱባቸው ችግሮች አሉ፡፡

ባጠቃላይ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ሂደት ተማሪዎች ከስነ ልቦናዊ እና ከግንዛቤ የሚመነጩ ችግሮች እንዳሉ ሆነው፤ከፊደል አጻጻፍ፣ከስርዓተ ነጥብ፣ከይዘት፣ከቃላት አመራረጥ፣ከዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ከአንቀጽአደረጃጀት አንጻር ልዩ ልዩ ችግሮች እንደሚስተዋልባቸው መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.4 በመጻፍ ትምህርት ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች

ምሁራን ጽህፈት ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ አእምሮአዊ ተግባር እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ አእምሯዊ ጥረትን የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑም ተማሪዎች አንድ ጽሁፍ ለመጻፍ በሚሞክሩበት ሰዓት በርካታ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ Byrne (1988) መጻፍን ከሌሎች ክሂሎች በተለያየ መልኩ አስቸጋሪ የሚያደርጉት ነጥቦችን በሶስት ከፍሎ ያስቀምጧቸዋል፡፡ የመጀመርያው ስነ-ልቦናዊ ችግር ነው፡፡ለምሳሌ በንግግር ጊዜ አድማጭ ከጎን ይኖራል፤በመጻፍ ሂደት ግን አንባቢ ከጎን የመኖሩ ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡በመሆኑም ጸሀፊው ቅጽበታዊ ምላሽ እንዲያገኝ በማወቅ ሀሳቡን በመጻፍ ለመግለጽ ይሞክራል፡፡በዚህም የተነሳ ጸሀፊው፣ አንባቢው ከጎኑ እንደሌለ በማሰብ ሀሳቡን በመጻፍ ለመግለጽ ሲሞክር የመጨነቅ ስሜትና ሌሎች ተያያዥ ስነ ልቦናዊ ችግሮች ሊፈጠሩለት ይችላሉ፡፡ ሁለተኛ ስነ-ልቦናዊ ችግር ነው፡፡
በንግግር ሂደት ለሰዋሰዋዊ ሁኔታዎች የመጨነቅ ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡ ነገር ግን የመጻፍ ክሂል ለሰዋሰው ሆነ ለተግባቦታዊ ሁኔታዎች ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ተጠንቅቆ መጻፍን ይጠይቃል፡፡ ሶስተኛው ግንዛቤያዊ ችግር ነው፡፡ ለአብነት ያህል ንግግር ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ለረጅም ሰአት ሀሳቡን በቀላሉ ለመግለጽ የሚያስችልበት ሁኔታ ይኖራል፤ ምንም እንኳን ግንዛቤ የራሱ የሆነ ድርሻ ቢኖረውም መጻፍ ግን በዋነኝነት በመማር የሚገኝ ክሂል እንደመሆኑ መጠን በቂ ግንዛቤ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ የጻፊው ግንዛቤ ከልላው ሀሳቡ ለመግለጽ የሚቸገርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ከዚው ጋር በተያያዘ Mohamed (2015) የተለያዩ ምሁራን በመጥቀስ እንደሚገልጹት ተማሪዎች በመጻፍ ትምህርት ሂደት ከፊል አጻጻፍ፣ ከስርአተ ትምህርት አጠቃቀም፣ ከይዘት ከቃላት አመራረጥ፣ ከአረፍተ ነገር አወቃቀር ከአንቀጽ አደረጃጀት ወዘተ……. አኳያ የሚከሰቱባቸው ችግሮች አሉ፡፡ በአጠቃላይ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ተማሪዎች ከስነ-ልቦናዊ፣ እና ከግንዛቤያዊ የሚመነጭ ችግሮች እንዳሉ ሁነው፤ ከፊደል አጻጻፍ፣ ከስርዓተ ነጥብ፣ ከይዘት፣ ከቃላት አመራረጥ፣ ከአረፍተ ነገር አወቃቀር ከአንቀጽ አደረጃጀት አንጻር ልዩ ልዩ ችግሮች እንዳስተዋልንባቸው መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.5 የመጻፍ ክሂል አስፈላጊነት

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱት አራቱም ክሂሎች የየራሳቸው አስፈላጊነት አላቸው፡፡ምንም እንኳን ሁሉም ክሂሎች ተናጥላዊ አገልግሎት ቢኖራቸውም ክሂሎቹ እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊዎች በመሆናቸው የአንዱ ክሂል መዳበር ለሌላኛው ክሂል መዳበር

አስተዋጽዖ አለው፡፡የመጻፍ ክሂልም የራሱ የሆነ አስፈላጊነት እንዳለው ሁሉ ለሌሎችም ክሂሎች መዳበር የራሱ አስተዋጽዖ አለው፡፡

የዘርፉ ምሁራን እንደሚገልጹት የመጻፍ ክሂል መዳበር በቋንቋ ላይ የሚኖርን ተግባቦታዊ ብቃት እጅግ ከፍ በማድረግ ፍላጎትን ለማሳካት ያስችላል፡፡እንዲሁም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ በመሆናቸው የመጻፍ ክሂል መጎልበት ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ጉልህ ፋይዳ እንደሚኖረው ሙሁራን ያሳስባሉ፡፡Byran (1988) የመጻፍ ክሂል የልምድ ሂደትና የክሂሉ መዳበር ከሚኖሩት በርካታ ስነ ትምህርታዊ ፋይዳዎች (pedagogical purposes) ያሏቸውን አምስት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ገለጸዋል፡፡ምሁሩ የገለጿቸው የመጻፍ ክሂል አምስት ስነ ትምህርታዊ ጠቀሜታዎቸዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጻፍ ተግባር ወይም ልምምድ ማካሄድ ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ የመማር ስልት ወይም ፍላጎት እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡በተጨማሪም ቋንቋን በንግግራዊ ዘዴ ብቻ በቀላሉ ለመማር የሚቸገሩ አንድ አንድ ተማሪዎች በቋንው እንዲያነቡ እና እንዲጽፉ ሲደረግ የበለጠ የደህንነት ስሜት ይፈጥርላቸዋል፡፡እንደነዚህ አይነቶቹ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለብቻቸው ሲገልጹ የበለጠ ነጻ የመሆንና የመዝናናት ስሜትን ሊፈጥርላቸው ስለሚችል መጻፍ እንደ ማነቃቂያ በመገልገል የተነሳሽነት ስሜታቸውን ሊጨምርላቸው ይችላል፡፡

2. መጻፍ የቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸውን ክህሎት መሻሻል ማሳየት አለማሳየቱን ለመረዳት የሚያስችላቸው ተጨባጭ መሳሪያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ይሁን እንጂ እውነተኛ የሆነ የችሎታው አመልካች ነው፡፡ ማለት ባይቻልም ስነልቦናዊ ፍላጎታቸውን ሊያመለክት ይችላል፡፡

3. የመጻፍ ክሂል መዳበር ከአንድ በላይ የመግባቢያ ክሂል (ከመናገር እና ማዳመጥ በተጨማሪ) እንዲኖር እና የውጭ ቋንቋን ( Foreign language) ለመማር ያስችላል፡፡በተለይም የተለያዩ ክሂሎች በትክክል ከተቀናጁ በአንድ ቋነቋ ብቻ ከሚጠቀሙ ሰዎች የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

4. መጻፍ የክፍል ውስጥ መልመጃዎችን ወይም ተግባራትን የተለያዩ አይነቶች እንዲሆኑ ማድረግ አሰልቺነትን ለማሶገድ ይረዳል፡፡ለምሳሌ በክፍል ውስጥ በንግግር ልምምድ ሂደት ጣልቃ በመግባት የእረፍት ጊዜ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን የማነቃቂያ ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡በአንጻሩ ደግሞ ከክፍል ውጭ ባለው የእለት ተእለት ማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚከናወነውን ተግባቦታዊ ሒደት መጠን ያሳድጋል፡፡

5. መጻፍ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የሙከራ ፈተኛዎችን ወይም መመዘኛዎችን ለመስጠት ይጠቅማል፡፡ይህም የመጻፍ ክሂልን ለመመዘን ብቻ ሳይሆን፤ሌሎች ክሂሎችንም(መናግርና ማዳመጥን) በተዘዋዋሪ ለመመዘን ያስችላል፡፡ እነዚህን ሌሎች ክሂሎች በቀጥታ መሞከር ቢቻልም የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥሙን ጽሁፋዊ የሙከራ ፈተናዎችን ተግባራዊ ልናደርጋቸው እንችላለን (Pp. 6-7)::

ከላይ የቀረቡት Byaran (1988) የገለጿቸው የመጻፍ ክሂል ዋና ዋና ስነ ትምህርታዊ ጠቀሜታዎች ናቸው፡፡

## 2.1.5.1 ውጤት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ

ይህ ዘዴ ከጽሁፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች የመጀመሪያው ሲሆን የሚያተኩረውም ተማሪዎች በሚጽፉት የመጨረሻ ስራ ላይ ነው፡፡አላማው በሚያከናውኗቸው የመጻፍ ትምህርት ተግባራት ትክክኛ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ ነው፡፡በመሆኑም የጻፏቸው ነገሮች ከሰዋሰው፣ከዐረፍተ ነገር ወቃቀር፣ከሀሳብ ቅንጅት፣ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ከግልጽነት ወዘተ አኳያ ይገመገማሉ፡፡በሌላ መልኩ Ricareds (1990) በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች በተለያዩ አንቀጾችና ጽሁፎች የመዋቅር ቅንብር ስልት ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ይመራቸዋል ይላሉ፡፡ምክንያቱንም ሲገልጹ የዘዴው  ትኩረት ተማሪዎች ስህተት የሌለበት ጽሁፍ እንዲጽፉ ማስቻል ስለሆነ የተፈለገውን የጽሁፍ ቅርጽ እንዲያጠኑ በማድረግ ወደፊት ታዘው በሚጽፉት ነገር ላይ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

የውጤት ተኮር ዘዴ አተገባበር ተማሪዎች ሞዴል ዓረፍተ ነገርን ደግመው እንዲጽፉ የሚጋብዝ መልመጃ መስጠት፣ አንዳንድ ጊዜም ከአንድ ነገር ቅርፅ ወደ ሌላ አይነት የዓረፍተ ነገር ቅርፅ የመቀየር ተግባራትን ለማከናወን የሚጋብዝ መልመጃ በመስጠት የሚተገበር መሆኑን Ricards(1990) ያብራራሉ፡፡ ዋናው ትኩረቱ በሰዋሰው፣ በቅርጽና በስርዓተ ነጥብ ከመሆን ባሻገር ተማሪዎች ስህተት የመፍጠር አጋጣሚ እንዳያገኛቸው ጥረት በማድረግ ረገድ ልዩ ሥፍራ ይሰጣል፡፡

## *2.1.5.2 ውጤት ተኮር አቀራረብ*

ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ አቀራረብ ተማሪዎቹ የመጨረሻ ስራዎቻቸዉን ለምዘና ከማቅረባቸዉ በፊት የሚከተሏቸዉ አራት ደረጃዎች አሉ፤፤   እነዚህም ፡-
ደረጃ 1. ማለማመድ (ማስተዋወቅ) እንዴት እደሚጽፉ፣ መከተል ያለባቸዉን አካሄድ መንገር፤ ለምሳሌ፡ የሚቀርብላቸዉ ሞዴል ስራ ወይም ጽሁፍ እንዲከተሉ በመምህር የሚቀርብ ገለፃ)

ደረጃ 2. ቁጥጥራዊ መጻፍ፡- (መስመር በመስመር፣ ወይም የተጠቀሟቸዉን ዐረፍተ ነገሮች መምህሩ እያየ አስተያየት ይሰጥባቸዋል፤ ርዕሰ መስጠትና ምን ያህል ዐረፍተ ነገሮች፣ አንቀጾች ወይም ገጽ መጻፍ እንዳለባቸዉ መንገርን ይጨምራል )

ደረጃ 3. ምሪታዊ መጻፍ፡- (በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ የተወሰነ ግንዛቤ አላቸዉ ተብሎ ስለሚታሰብ መምህሩ አቅጣጫ በመጠቆምና ምሪት በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ)

ደረጃ 4.ነፃ መጻፍ፡- (ተማሪዎች የተማሯቸዉን ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ከግምት እያስገቡ እንደሚጽፉ ተስፋ በማድረግ የፈለጉትን ርዕስ መርጠዉ በቻሉት የርዝማኔ መጠን እንዲጽፉ ነፃነት ይሰጣቸዋል፤ በዚህ ጊዜ የጽሁፉ ስራዎቻቸዉ የተማሩትን ሰዋሰዋዊ ስርዓቶች ስለመተግበራቸዉ እየታየ ምዘናዉ ይካሄዳል ማለት ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ዉጤት ተኮር አቀራረብ የሚቀርበውን ሞዴል ጽሑፍ ትኩረት የተሰጠባቸዉ የቋንቋ ገጽታዎችን ኩረጃና መልሶ በመጠቀም ላይ የሚያተኩር ሲሆን ትኩረቱም ይበልጥ የሚሆነዉ ከሚነሱ ሀሳቦች (ቁም ነገሮቹ) የተቀናጁበት መንገድ ላይ ነዉ፤ አጽንዖት ለመጨረሻዉ ዉጤት (ጽሑፍ) ይሰጣል ፤ በግል ወይም በተናጥል መስራትን የሚበረታታ ሲሆን ተደጋጋሚ ሙከራን አያበረታታም(እንዴ የጻፉትን ብቻ ይመዝናል)

ጽህፈትን በማስተማር ረገድ ውጤት ተኮር አቀራረብ ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም መምህር ተኮር ነው፡፡በዚህ ዘዴ ተማሪው ሞዴሎችን እንዲቀዳ ይበረታታል (Brakan,2003;Gabrielatos,2002)::ይህ ዘዴ በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ እስከ 1970 ዎቹ ድረስ ብቸኛው የማስተማሪያ ስልት ሆኖ አገልግሏል፡፡ የውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ጽሁፎች ምሳሌ ይሆናሉ፤ጥሩ ተጽፏል ተብለው የሚታሰቡ ጽሁፎችን አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣የአጻጻፍ ስልትን ወዘተ… ተንትኖ ማሳየት እና ተማሪዎች የተመለከቱትን በጽሁፋቸው እንዲተገብሩ በማድረግ ስልትን የሚከተል ሲሆን ዋነኛው ትኩረቱ የቋንቋውን ሰዋሰው ማስተማር ነው (pica,1986:6)::

የውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀጾችና አውዶች መዋቅር እና አደረጃጀት ላይ ነው፡፡አላማው ትክክለኛ ጽሁፎችን ማፍለቅ ነው፡፡የውጤት ተኮር አቀራረብ ዋና ዋና ባህሪያቱን እና መርሆቹን Richards( 2002:30-32) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

1. የድርሰት አጻጻፍ መመርያዎችን እና ህጎችን በተለያዩ የድርሰት አይነቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማሳየት ተማሪዎች በተግባር አደሚለማመዱቸው የደርጋል፡፡

2. የጽህፈት አላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸውን ጽሁፎች መጻፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡ በተለያዩ የድርሰት አይነቶች ቅርጽ እና አደረጃጀት ላይ ያተኩራል፡፡

3. ትክክለኛ የአረፍተ ነገር መዋቅር መሰረት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የሰዋሰው ችሎታ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል፡፡

4. ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲጽፉ እና ስህተት እንዳይሰሩ ይሞክራል፡፡

5. የእጅ ጽሁፍ፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት አገባብ፣ የፊደል አጣጣል ወዘተ... እውቀት በትምህርትነት ይቀርባሉ

ውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በስተመጨረሻ በሚያቀርቡት ስራ ላይ በመሆኑ ስህተት እንዲፈጽሙ አይፈቀድም፡፡አላማው ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ትክክል ሁነው እንዲገኙ ማድረግ ነው፡፡ (Ferris and Hedgcok 2005)፡፡ ስለሆነም ይህንን አቀራረብ በመከተል የመጻፍ ትምህርት በሚቀርበበት ወቅት ተማሪዎች በጽሁፍ ሂደት የሚያልፉበትን ደረጃዎች በመከታተል ትክክለኛ ጽሁፍ እንዲጽፉ ደርጋል፡፡ ተማሪዎች ፈጥረው እንዲጽፉ ያደርጋል፡፡ (Richard, 1990 ; Harmer, 2001 ; Williams, 2014) ብዙ ግዜ መምህሩ የመጻፍያ ርእስ ወስኖ የሚያቀርብበት ሲሆን ባዶ ቦታ መሙላት ዐረፍተ ነገር መመስረት፣ አረፍተ ነገር ማስፋፋት የመሳሰሉት የተለመዱ ተግባራት ናቸው (Raimes, 1983; Willams, 2014) ፡፡

ውጤታዊ አቀራረብን ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር ስንመለከተው ትኩረት የሚያደርገው በስተመጨረሻ ተጠናቆ በሚቀርበው ረቂቅ ላይ ሲሆን በእርማት አሰጣጡ ወቅትም ከጽሁፍ ይዘት ይልቅ ቅርጽ ላይ ያተኩራል(Silva, 1990; casanaue, 2013)፡ስለዚህ በዚህ ዘዴ ለሰዋሰዋዊ ችሎታ ትልቅ ግምት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም በዚህ አቀራረብ የመምህሩ አስተዋጽኦ ከተማሪው ሚና አይሎ የሚታይ ከመሆኑም በላይ ሂደቱን በበላይነት የሚቆጣጠርና ስህተቶችንም በማረም ረገድ በዳኝነት ስራ የሚከናወነው በመምህሩ ነው፡፡ በተቃራኒው ተማሪዎች ከመምህሩ የተሰጣቸውን ትእዛዝ በመቀበል የበላይነት አይሎ የሚታይበት ስለሆነ አቀራረቡ መምህር ተኮር አቀራረብ(Teacher centered) በመባል ይጠራል (White,1980; Richards, 1990; Harmer, 2004 )::

በዚህ አቀራረብ የመጻፍ ችሎታን ለማሳደግ ለተማሪዎች መነሻ የሚሆን ሞዴል ጽሁፎች ሳይቀርብላቸዋል፣ የቀረበላቸውን ሞዴል የቅርጽ የይዘትና አደረጃጀት ባህርያት ይማራሉ፣ ሰነ-ልቦናዊ ጉዳችንና ቅንብራዊ አስተዳደሮችን ይለያሉ የቀረበላቸውን ሞዴሎች ካጠኑና የቋንቋውን አለባውያን ከለዩ በኋላ አስመስለው እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡

በውጤት ተኮር አቀራረብ የመጻፍ ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች አሳማኝ ጽሁፎችን እንዴት እነደሚጽፉ ገለጻና ትረካ ስለሚደረግላቸው፣ ለእያንዳንዱ የጽሁፍ አይነት ምንም አይነት የቃላትና የአረፍተ ነገር አወቃቀር መጠቀም እንዳለባቸው ስለሚገልጽላቸውና የቋንቋ ችሎታውን ከፍ ለማድረግ ስለሚጥሩ ከመምህራን የሚጠበቅ ዋና ተግባር የተማሪዎችን የቋንቋ ስህተት ፈልጎ ማውጣት ነው፡፡

(Tangerpermpoon, 2008):: ስለዚህ በውጤት ተኮር የጽህፈትን ማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ የሚለካ በዲስኩር (በዓረፍተ ነገር) ደረጃ የተሰጡ ስራዎችን ተከትሎ ትክክለኛ የቋንቋ ቅርጾችን ማዘጋጀት ነው፡፡ ስለዚህ ሰዋሰዋዊ ችሎታ ትልቅ ትኩረት ወይም ግምት ይሰጠዋል፡፡ እናም ትክክለኛ የሆነ የዓረፍተ ነገር መዋቅር የጽህፈት አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ (Wihite, 1980 Richards, 1990)::

ውጤታዊ አቀራረብ(Product approach) ከረጅም ግዜ አንስቶ ጽፈትን ለማስተማር ሲያገለግል የኖረና በሁኑ ጊዜ በተላያዩ አላማዎች በማገልገል ላይ ያለ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በጽሁፍ የመጨረሻ ውጤትና በቋንቋው ቅርጽ ላይ ነው (Wihite, 1980 Richards, 1990):: ይኸውም ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ጽሁፎች በሞዴልነት አቀርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችን ፣ አደረጃጀትን ፣ የአጻጻፍ ብልህትን ወዘተ በማሳየት ተማሪዎች እነዝያኑ አስመስለው እንዲጽፉ የሚያለማምድ ነው (NUnan 1989 and Richard 1990)::

በዚህ አቀራረብ ጽህፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህም ተግባራት ውስን ጽህፈት ፣ መር ጽህፈት እና ነጻ ጽህፈት ደረጃዎች ናቸው፡፡

ውጤታዊ አቀራረብ ጽህፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ከእነዚህም ተግባራት ውስን ጽህፈት(Controlled Wraiting) ፣ መር ጽህፈት(Guided wraiting) እና ነጻ ጽህፈት (Free wraiting) ደረጃዎች ናቸው (Pincas 1982; Raimes, 1983, 7; Richards, 1990; 107)፡፡ የመጻፍ ተግባራት ሲገለጹ በወጥነት ላይ ያተኮረ የጽፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ መልመጃዎች ሁልጊዜ የሚጀመሩበት በውስን ጽህፈት መልመጃ

ነው፡፡ከዚያም ቀስበቀስ ወደ ነጻ የጽሁፍ ክሂል መልመጃ ያመራሉ፡፡እነዚህም የመልመጃ አይነቶችም የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

በአጠቃላይ የውጤት ተኮር  የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ድርሰቶችን በማረም እና ተማሪዎች ስህተት እንዳይሰሩ በመቆጣጠር ላይ ነው፡፡በዚህ የጽሁፍ ትምህርት አቀራረብ የተለያየ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣አንቀፆችን መገንባት እና ድርሰቶችን መጻፍ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ የሚደረጉ ልምምዶች፣ የሚመረጡ ሞዴሎች እና የዐረፍተ ነገሮች አመሰራረት የሰዋሰው ህግጋትን  የተከተሉ ናቸው፡፡

እንደ Rischards(2001:107), Pincas (1982:14),Raims (1983:7) አገላለጽ በውጤታማ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡እነዚህ ተግባራት ውስን መጻፍ(Controlled Writing) ፣መር መጻፍ(Guided Writing) እና ነጻ መጻፍ (free writing) ናቸው፡፡

### ሀ. ውስን ጽህፈት

በመጀመርያ ደረጃ የቋንቋ ተማሪዎች ለሚካሄድው የጽህፈት ትምህርት የሚቀርብ እና የውስንነት ደረጃው ፍጹም (አንጻራዊ) የሆነ ክንውን ነው፡፡ የዚህ ጽህፈት ዋና አላማ ተማሪዎች ንጽጽራዊ በሆነ መንገድ ከስህተት የጸዳ ጽሁፍ እንዲጽፉ ለተማሪዎች እድል  እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡

በውስን ጽህፈት ደረጃ ጽህፈትን ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች ውስን ማሰብንና ማፍለቅን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በውስን ቃላትን በማስተካከል ዓረፍተ ነገርን መስራት ፤ በአንቀጽ ውስጥ የቁጥር፣ የጾታ፣ የግዜ ወዘተ ለውጥ በማድረግ እንደገና መጻፍ ይገባቸዋል(Doff, 1988 እና Kroll)፡፡

### ለ. መር ጽህፈት

መር ጽህፈት በውስን እና በልቅ ጽህፈት መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ የኽውም ተማሪዎች በውስን ጽህፈት ደረጃ ካዳበሩት መሰረታዊ የዓረፍተ ነገር አጻጻፍ ክሂል በተጨማሪ የአጻጻፍ ስልት ለመለየት የሚያግዝ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች መምህራን በሚያቀርቡላቸው ሞዴል መሰረት የጽህፈት ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚደረጉ ውይይቶች ድርሰት ለመጻፍ የሚያገለግሉ መር የጽህፈት ተግባራት መሆናቸውን Doff (1988, 62) Raimes (1983, 103) እና Princas (1982, 102) ይገልጻሉ፡፡

በመር ጽህፈት የሚቀርቡትን ተግባራት Raimes (1983 ፤103) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

- በሰንጠረዥ የሚቀርቡ ሀሳቦችን ወደ ጽሁፍ መቀየር፣
- በጅምር የቀሩ ጽሁፎችን (ውጥን ታሪኮችን፣ ደብዳቤዎችን ፣ቅርጾችን ወዘተ) መጨረስ፣
- የተዘጋጀ ቢጋር ተጠቅሞ አንቀጽ መጻፍ፣
- የቀረቡትን ነገሮች በማወዳደርና በማነጻጸር በጽሁፍ መግለጽ፣
- ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ለጥያቄዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መነሻ አድርጎ አጭር ታሪክ መጻፍ፡፡

ሐ. ነጻ ወይም ልቅ ጽህፈት

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በአብዛኛው መምህራን በሚሰጧቸው ወይም ራሳቸው በመረጡት ዙርያ ሀሳብ አፍልቀው በራሳቸው ቋንቋና አገላለጽ ድርሰት የሚጽፉበት ነው(Pincas, 1982 እና Raimes 1983)፡፡ድርሰት የመጻፍ ስራ የሚጀምረው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ቅርጾች በመለማመድ ነው፡፡ ከልምምድ ቀጥሎ ለሚጽፉት የድርሰት አይነትና ሞዴል ይቀርባል፡፡ ነጻ ጽህፈት ለሰዋሰዋዊ አጠቃቀም እና ለስርአት አጻጻፍ ትኩረት የሚሰጥ እንዲሁም በትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የሚገልጹበት እድል ይሰጣል፡፡ Raimes (1983 7) ነጻ ጽህፈት ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚጽፉበት ደረጃ ቢሆንም የጽሁፋቸው መለኪያ ምን፣ እንዴት፣ ለማን እና ለምን ተጻፈ? የሚሉ ጥያቄዎችን ሳይሆኑ የሚነሱ ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ቀረበ ወይ የሚለው ነው፡፡በመሆኑም የተማሪዎቹ ትኩርት የሚያርፍው ሀሳባቸውን በመግለጽ ላይ ሳይሆን በጽሁፋቸው ጥራት ወይም ንጽህና ላይ ነው፡፡ /Byren,1991;16 Pincas,1982/

በውጤት ተኮር አቀራረብ የጽህፈት ማስተማር ዘዴ የመምህሩ ሚና በአብዛኛው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህጎችን ማስተማር፣ የተማሪዎች የመጨረሻ ውጤት ሰብስቦ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችንና የአጻጻፍ ስርዓት ግድፈቶችን ማረም፣ የጽሁፉን ጥሩነትና መጥፎነት ከትክክለኛነት አንጻር መገምገም ፣ ለመማር የሚያበረታታ አስተያየት ወይም ውጤት መስጠት ነው፡፡

በውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች ቀርበው ከመተግበራቸው በፊት ተገቢነታቸውን፣ ቀስቃሽነታቸውን፣ ግልጽነታቸውና ለአውዱ ተገቢ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ መልመጃዎች ግልጽ መመርያ የላቸውን እና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ቅንጅት ያላቸው መሆኑን ያሳውቃል፣ ቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት ለተማሪዎች ለማሳወቅ በጽሁፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፣ ተማሪዎች ለጽህፈት ትምህርት ቅድመ ዝግጅቶች የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

### 2.1.5.3 ኢ.ርቱእ (indirect) የጽህፈት ምዘና

ኢ.ርቱእ (indirect) የምዘና ዘዴ አንዳንድ ጊዜ ምርጫ ነክ ምዘና ተብሎ ይጠራል ፡፡ ተፈታኙን እንዲጽፍ የሚጠይቅ ሳይሆን ፤ በምረጫ ነክ ለቀረቡልት ጥያቄዎች ምላሽ እዲሰጥ ብቻ የሚጠይቅ ነው (Stiggins, 1982) ፡፡ ኢ.ርቱእ (indirect) ምዘና ስለውጤታማ ጽህፈት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ያጠቃቀም ስርአቶች እንደ ሰዋስው፣ ስርአተ ነጥብ፣ አረፍተነገር ምስረታ፣ አወቃቀርና ሌሎችን አጠቃቀሞችን የተገነዘቡ መሆናቸውን የሚመዝን መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህ ዘዴ በሌላ መልኩ የአንድን ተማሪ የጽህፈት ችሎታ ለመገምገም የሚያስችል አስፈላጊ ግን ደግሞ በቂ ያልሆነ መረጃ ይሰጣል፡፡

በኢ.ርቱእ (indirect) የምዘና ዘዴዎች ተማሪዎቾ የመጻፍ ስራን ወይም የመድረስ ሂደት እዲያከናውኑ አይጠየቁም ፡፡ በሌላ አገላለጽ በእንደዚህ አይነት ምዘናዎች የቋንቋ ህጎችና የአጻጻፍ ስርአቶች ይመዘናሉ፡፡ እንደ Heaton (1988) ገለጻ በቃል መጻፍን ፣ ቃላትን አስተካክሎ መጻፍና ተገቢ ቃላትን መርጦ የመጠቀም ችሎታን የሚጠይቁ በምርጫ መልክ ጥያቄዎችን ፣ጅምር አረፍተ ነገሮችን ማሟላትን ፣ ወዘተ በኢ.ርቱእ (indirect) ምዘና አይነት ውስጥ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ተጨባጭነት ባለው ፣ ፈጣንና አስተማማኝነት ባለው ሁኔታ ለማረም ምቹ ናቸው፡፡ Tribbe (1996) በተመሳሳይ ሁኔታ ኢ.ርቱእ (indirect) የጽህፈት ምዘና በምርጫና በዝግ የፈተና አይነቶች አማካኝነት አንድ ተፈታኝ በአረፍተ ነገር ደረጃ የአረፍተ ነገሮችን ሰዋስዋዊ ስህተቶች፣ የፊደልና የስርአተ ነጥብ ጉድለቶችን እንዲያስተካክሉ የሚጠይቅ ነው በማለት ገልጸውታል፡፡

በኢ.ርቱእ (indirect) ምዘና ላይ የሚነሱት ችግሮች ውስጥ አንዱ ጸሀፊዎች ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዴት መመስረት እንደ ሚችሉ መረጃ መስጠት አዳጋች መሆኑ ነው (Weir, 2005) ፡፡ ሁለተኛውና በተደጋጋሚ በኢ.ርቱእ ምዘና ላይ ሚሰነዘረው ትችት ፣ አሉታዊ ተጽእኖ ማስከተሉ ነው፡፡ ተማሪዎች እንዲያዳብሩ የሚፈለገው ትክክለኛ ክንውን እዲለማመዱ እድል አይሰጥም (Bailey, 1998) ፡፡ ሶስተኛ ከባድ ትችት በኢ.ርቱእ የጽህፈት ምዘና ላይ የደረሰው ከአግባብነት አኳያ ሲታይ ነው፡፤ ሁሉም ተመራማሪዎች ርቱእ እና ኢ.ርቱእ ምዘናዎች ብዙውን ጊዜ አንድም በከፍተኛ አልያም በመካከለኛ ሁኔታ እንደሚዛመዱ የተለያዩ ስራዎች አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ግኝቶች ኢ.ርቱእ ምዘና በተሟላ ሁኔታ የጽህፈት ችሎታን የሳያል አላሉም፡፡ ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ ኢ.ርቱእ ምዘናዎች የጽህፈት ችሎታን በትክክል ማሰየት አለመቻላቸው ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ ሁለቱን በጥምረት መጠቀምና የሚይዙትንም የውጤት መጠን ማሳወቅ የሚሻል እንደሆነ ይመከራል፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ፈተና ውስጥ

ሊኖሩ የሚገባቸው የኢ.ርቱ እና የርቱእ ጥያቄዎች መጠን ግን እስካሁንም ድረስ ለክርክር ክፍት ነው (Koffler, 1984 )፡፡

### 2.1.5.4 ርቱእ (direct) የጽህፈት ምዘና


ርቱእ የጽፈት ምዘና ዘዴ የተማሪዎችን የጽፈት ችሎታ በጻፏቸው ጽሁፎች አማካኝነት መመዘኑ ላይ ያነጣጥራል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዲህ አይነቱ ምዘና ተማሪዎች መረጃን እዲተነትኑ፣ እዲያጠቃልሉ፣ በአዲስ መልክ እዲያደራጁና እዲገመግሙ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ተመራጭነት እያገኘ ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ርቱእ የጽፈት ምዘናዎች ከኢ.ርቱእ የጽፈት ምዘናዎች በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ ስለሚለኩ በብዙ የትምህርት ተቋምት ተመራጭ እየሆኑ መጥተዋል ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን ጹሁፍ እንዲያሻሽሉ ያበረታታሉ ከዚህም በላይ ርቱእ ምዘናዎች እውናዊ (Authentic) በመሆናቸው ጠቃሚ ናቸው፤ ምክንያቱም አብዛኞቹ ተግባራት የገሀዱን አለም የሚወክሉ ናቸው፡፡ ርቱእ የጽህፈት ምዘናዎች ሁሉም የጽህፈት አለባዉያን አዋህደው የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም በርቱእ የጽህፈት ምዘና አማካኝነት አንድ ጻሀፊ ምን ያህል ጥሩ ጻሀፊ ወይም በጽሁፍ አማካኝነት ምን ሊያከናውን እነደሚችል መግለጽ ይቻላል (Weir,1993) ፡፡

ርቱእ የጽህፈት ምዘናዎች በሁለት አይነት መንግድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ነጻ ጽህፈት (free writing) እና ግድብ ጽህፈት (control writng) ተግባራት ናቸው (Weir, 1990 ፤ Weir, 1993 ፤ Coomble et al , 2007)፡፡ ነጻ የጽህፈት ተግባር ተፈታኞቹ የቀረበውን ጥያቄ ያነቡና ዳራዊ እውቀታቸውንና ከኮርሱ የተማሩትን እውቀት በማጣመር የታቀደ ምላሽ እንዲሰጡ ይጠይቃል፡፡ ግድብ ጽህፈት (control writng) ተግባር ደግሞ በጥያቄው ውስጥ የቀረበውን ይዘት (በአብዛኛው በቻርት ወይም በዲያግራም መልክ የሚቀርቡ መረጃዎችን ) በመጠቀም እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው (Soombe et al ; 2007)፡፡

ኢ.ርቱእ ምዘና ከፍተኛ አስተማማኝነት ያለው ፣ ለመፈተንና ለማረም የሚቀል ሲሆን ፣ ርቱእ የምዘና ስልት ደግሞ ከፍተኛ አግባብነት ያለው እውናዊ ተግባቦትን የሚያንጸባርቅ ፣ የጽህፍት ችሎታን በቀጥታ የሚለካ ፣ ሁሉንም የጽህፈት አላባዎች አቀናጅቶ የሚይዝ ነው ከበለጠ ያእቆብ(2006)

## 2.2.ጥናቱ የሚከተለው ጽንሰ ሀሳባዊ ማእቀፍ

ይህ ጥናት በዋነነት ትኩረት የሚያደርግባቸው ነጻ እና ጥገኛ ተለዋዋጮቸ ያላቸውን የእረስ በርስ ዝምድና የሚያሳይ እና የጥናቱ አካሄድ የሚያሳይ አጠቃቀም ጽንሰ ሀሳባዊ መአቀፍ መግለጫ ነዉ፡፡




ከላይ የቀረበው ስእላዊ በግለጫ የሚያመለክተው የቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው አላማዎች አንዱ ክሂሎችን ለማዳበር ሲሆን ከአራቱ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ደግሞ የመጻፍ ክሂል ነው፡፡ ይህን የመጻፍ ክሂል ደግሞ ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን እንጠቀማለን፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አላማ ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ የሚፈተሽ ሲሆን የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች በቅድመ እና በድህረ ፈተና የሚያመጡት ውጤት መኖሩን ከዚህ በላይ በተቀመጡት ሳጥኖች የእርስ በእርስ

ግንኙነታቸውን እንረዳለን፡፡ ጥናቱ የሚከተለው ንድፍ ከፊል ፍትነታዊ በመሆኑ የተማሪዎች ቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤት እነለይበታለን፡፡

## 2.6 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ትኩረታቸውን የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎችና የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ አድርገው የተሰሩ በርካታ የሀገር ውስጥ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ሆኖም ግን በጥናቶቹ የተገኙ ውጤቶች ወጥነት አይስተዋልባቸውም፡፡ይህም የሚያሳየው ዘዴዎቹ ለተማሪዎች የጽህፈት መዳበር ያላቸውን አስተዋጽኦ በተመለከተ በቂ የሆነ ጥናት ሊጠና ባለመቻሉ ነው፡፡በዚህ ንዑስ ርዕስም ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸው ሶስት ጥናቶች ይዳሰሳሉ፡፡ የመጀመሪያው ጥናት በማሬ (2011) የተሰራው ጥናት ነው፡፡ጥናቱ የተከናወነው በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ማሚያ ጥናት ሲሆን "ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ (በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት )"ላይ የተካሄደ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተግባር ላይ የዋለ ሲሆን፣ አጥኚዋ በሁለት ቡድን ከፊል ሙከራዊ ንድፍ ተግባር ላይ አውላለች፡፡ ይህ ጥናት የተካሄደበት ቦታ ጎንደር ከተማ አስተዳደር ሲሆን ቦታው በአመቺ ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል፡፡ መረጃውን ለመሰብሰብ የተጠቀመችበት ስልት ፈተና ነው፡፡ መረጃዎቹ የተተነተኑበት ስልት በባእድ ናሙና ቲ- ቴስት ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው በቅድመ መጻፍ ክሂል በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳልታየ የተገኘው ውጤት አመልክቷል፡፡ በድህረ ፈተና ውጤት ደግሞ የተሻለ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ስለዚህ ችግር ፈቺ የማስተማርያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል አስተዋጥኦ አለው፡፡

ሁለተኛው ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የመስታወት (2014) ጥናት ሲሆን ርዕሱም "(ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር እና ተነሳሽነት ለመፈጠር ያለው ሚና በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን በፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)"የሚል ነው፡፡ጥናቱ የተከናወነው በጅማ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር

ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያነት ሲሆን ተግባር ተኮር የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ አፈፊት ያልሆኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ያለውን ሚና መመርመር የሚል አላማ ነበረው፡፡ይህን አላማ ለማሳካትም አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ፍትነት መሰል ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡በጥናቱም ተግባር ተኮር የቋንቋ አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋኦ አለው፡፡

የመስታወት (2014) ጥናት የቋንቋ አቀራረብ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መዳበር ያለውን አስተዋጽዖ የመረመረ ጥናት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ሆኖም ግን ሁለቱ ጥናቶች

ትኩረት ያደረጉባቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች የተለያዩ መሆናቸው የጥናቶቹን ልዩነት ያመለክታል፡፡በመሆኑም በመስታወት ጥናት ተነጥሎ ያልተሞከረው ውጤት ተኮር አቀራረብ በዚህ ጥናት በተናጥል ተሞክሮ በመስታወት ጥናት የተስተዋለው ክፍተት ይሞላል፡፡

ጽህፈት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሲሆን የሰው ልጅ ሀሳቡንና ስሜቱን ለመግለጽ ፣ መልእክት ለማስተላለፍ ፣ በአለም ላይ የሚፈጸሙ ሁነቶችን በተመለከተ መረጃ ለመለዋወጥ ፣ ስለራሱም ሆነ ስለሌሎች በጥልቀት ለመረዳት፣ ባህልን፣ ወግንና ታሪክን በሰነድነት በማስቀመጥ ለመጭው ትውልድ ለማቆየት የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ Heawan (2005) ፣ Miller (1999) ፣ Hedge (1998) እና Riamis (1983) በመጥቀስ ገልጽዋል፡፡

ይሁን እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ክሂል ትምህርት ትኩረት እንዳነስውና በዚህም ረገድ የተማሪዎች የጽህፈት ችሎታ ደካማ እንደሆነ (ማረው ፣ 2005 ፣ አምሳሉና ደምሴ ፣ 1982 ፣ አለማየሁ ፣ 1986 ፣ ደረጀና ግርማ ፣ 1999) ገልጸዋል፡፡

የመጨረሻው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆነው ጥናት በተካልኝ (2009) ተሰራው ጥናት ሲሆን ሂደት ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እና አመለካከት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ በምዕራብ ሸዋ አከባቢ በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት የሚል ርዕስ አለው፡፡ጥናቱ የተከናወነው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲበ በተግባራዊ ስነ ልሳን ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት ሲሆን ተቀዳሚ አላማው የሂደተዘውጋዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር የሚል ነው፡፡ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ሂደተዘውጋዊ የመጻፍ

ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡የተካልኝ ጥናት ይህ ጥናት በጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ላይ ማተኮራቸው ያመሳስላቸዋል፡፡በአንጻሩ ደግሞ የተካልኝ ሥራ ያተኮረው ሂደተዘውጋዊ ዘዴ ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ውጤት ተኮር ዘዴ ላይ ነው፡፡በመሆኑም በተካልኝ በተናጥል ያልተዳሰሰው ውጤት ተኮር አቀራረብ በዚህ ጥናት ተዳሶ በተካልኝ ጥናት የታየበት ክፍተት ይሞላል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

በምዕራፍ አንድ ስር እንደተገለጸው የዚህ ምዕራፍ አብይ አላማ ውጤት ተኮር የጽፈት ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት መለየት ሲሆን የተጠቀሰውን አላማ ከግብ ለማድረስም ከጥናቱ አይነት አንጻር ይህ ጥናት አይነታዊ እና መጠናዊ(ቅይጥ) ነው፡፡ ከጥናት ንድፍ አንጻር ደግሞ ከፊል ሙከራዊ (Quasi Expermental) የምርምር ንድፍ በመከተል የተከናወነ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ መረጃ የተሰበሰብበት እና የተተነተበት መንገድ መጠናዊ ዘዴን በመገልገል ነው፡፡ በዚህም የሁለቱን ቡድን ቅድመ ትምህርት ጽህፈት እና ድህረ ትምህርት ጽህፈት ፈተና የአጠናን ዘዴ ተግባር ላይ አውሏል፡፡

የጥናቱ አይነት አይነታዊ እና መጠናዊ የሆነበት ምክንያት ለጥናቱ በግብአትነት የሚያገለግሉት መረጃዎች አይነታዊ እና መጠናዊ በመሆናቸው ነው፡፡ይህ ማለት ለዚህ ጥናት የሚያገለግሉት መረጃዎች የሚሰበሰቡት በፈተናዎች ሲሆን የፈተናዎቹ ውጤትም በቁጥር የሚገኝ ነው፤ ይህም የጥናቱን አይነት አይነታዊ እና መጠናዊ አድርጎታል፡፡

## 3.2. የናሙናዎች አመራረጥ ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽዖ ለመመርመር ሲሆን፡፡ ይህንን ለማሳካት የተለያዩ ናሙናዎች ለመጠቀም ተችሏል፡፡ ናሙናዎችም የጥናቱ ቦታ፣ ተጠኚ ተማሪዎች እና የመጻፍ ክሂል ትምህርት የዘቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ናናዎች የሚመረጡባቸው የናሙና አመራረጥም የሚከተለውን ይመስላል፡፡ሁለቱ ቡድኖች የቁጥጥር ቡድን እና የሙክራ ቡድን በሚል ተሰይመዋል፡፡

በመቀጠልም ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን አንድ አይነት ቅድመ ትምህርት የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ይህም ዳራዊ የጽህፈት እውቀታቸውን ለማወቅ ከማስቻሉም ባሻገር በተመሳይ ደረጃ ላይ መገኘት አለመገኘታቸውንም ለመለየት እና ቀጣይ እርምጃ ለመውሰድ መንገድ የሚከፍት ይሆናል፡፡ከዚያም የሙከራ ቡድኑ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማርያ ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በመደበኛ ማስተማር ዘዴ የጽህፈት ይዘቶቹን እንዲማሩ ይደረገና በመጨረሻም ሁለቱ ቡድኖች አንድ አይነት ድህረ ትምህረት

የጽህፈት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡በተያያዘ መልኩም ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ የምርምር ዘዴ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የቅድመ እነና ድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት ውጤታቸውን ለመፈተሸ ተሞክሯል።

ይህ የአጠናን ዘዴ ሁለት ተተኳሪ ቡድኖችንም ሳይማሩ በሚወስዱት ፈተና እና በውጤት ተኮር የጽፈት ማስተማርያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በሚዎስዱት ፈተና የሚያሳዩት የችሎታ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክት ነው። Qasim et al.(2014) እንደሚገልጹት የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ስልት የማስተማሪያ ዘዴ ሙከራዊ በሆነ መልኩ ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ በሁለት ተተኳሪ ቡድኖች መካከል የታየ የውጤት ልዩነት ተገምግሞበታል፡፡

## 3.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተሳታፊ የሚደረጉት ተጠኚዎች በአመቺ ናሙና አመራረጥ ስልት የሚመረጡ ሲሆን በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልልላዊ መንግስት በቡኖ በደሌ ዞን በበደሌ ከተማ እንጊቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት ለጥናቱ እንዲመረጥ ተደርጓል፡፡ ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ዋንኛ ምክንያት ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን የትምህርት ቤቶችን ልዩ ትብብር እና ሌሎች ድጋፍ የሚያስፈልጉ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚጠይቅ በመሆኑ እና ተመራማሪው እነዚህን ድጋፎች ከትምህርት ቤቱ ውስጥ እንዲያገኝ ማሰብ በመቻሉ እና ለአጥኚው የስራ ቦታው በመሆኑ የምርምሩን ሂደት በቅርበት ለመከታተል እንዲያመች በማሰብ ተመርጧል፡፡

## 3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ

በዚህ ጥናት የተካተቱት ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ውስጥ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡት በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ነው፡፡ይህ የክፍል ደረጃ የተመረጠበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጡት በዘጠነኛ ክፍል ሲሆን ለትምህርት ቤቱ አዲስ እንደመሆናቸው መጠን መረጃውን በትክክል አይሰጡም ከሚል እሳቤ ነው፡፡አስራ አንደኛ እና አስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን ካለመምረጣቸው የተነሳ ትምህርቱን አይማሩትም፡፡ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ ከተመረጠ በኋላ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ስድስት የአስረኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ ሁለቱ በቀላል የእጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት አስረኛ "B" ምድብ የመማሪያ ክፍል እና አስረኛ " F " ምድብ የመሪያ ክፍል ተካተዋል፡፡ ተማሪዎች ከተመረጡ በኋላ በሁለቱ

ምድቦች ውስጥ የተካተቱ ተማሪዎች ተመጣጣኝ የመጻፍ ችሎታ እንዳላቸው ለማረጋገጥ በክፍል ውስጥ ለመለያ በተዘጋጀው ፈተና አማካኝነት 100% በመውሰድ የ "B" ምድብ አማካይ ውጤት 53.7778 ሲሆን የ "F" ምድብ ደግሞ 50.2571 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የተመዘገበው ውጤት በባዕድ ቲ-ቴስት የተፈተሸ ሲሆን የተገኘው ቲ-ቴስት ውጤት -1.539 እና የጉልህነት ውጤት መፈተሻ ቡድን ሌላኛውን ምድብ ደግሞ የቁጥጥር ቡድንነት ተመድበዋል፡፡ ሁለት ምድቦች በእድል ሰጪ ናሙና ተመርጠዋል፡፡በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድን ለመመደብ ቀላል የዕጣ ንሞናን መጠቀም ያስፈለገው አመዳደቡ ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ስድስት የአስረኛ መማሪያ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡በውስጡም 178 ወንድ 200 ሴት በድምሩ 378 ተማሪዎች የሚማሩ ሲሆኑ በእያነዳንዱ ምድብ ማለትም "B" ወንድ 13 ሴት 17 በድምሩ 30 ተማሪዎች በሁለተኛው ምድብ ማለትም "F" ደግሞ ወንድ 14 ሴት 16 ድምር 30 ተማሪዎች ሲመረጡ ከሁለቱም ምድቦች በአጠቃላይ ወንድ 27 ሴት 33 በድምሩ በሁለቱም ምድቦች 60 ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ መረጃው ከ62 ተማሪዎች (ወንድ 13 ሴት 17) እጣ በማውጣት አስረኛ"B" በሙከራ ቡድን ፣ አስረኛ "F" ከ65 ተማሪዎች (ወንድ 14 ሴት16) ደግሞ በቁጥጥር ቡድን በመመደብ የሙከራ ትምህርት ተከናውኗል፡፡

### 3.2.4 የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ

*ይህ ጥናት ተዛምዷዊ ጥናት ሲሆን ዋና ትኩረቱም ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ መመርመር ነው፡፡ ዘዴውና የተማሪዎቹ ውጤት ያላቸውን ተዛምዶ ለመፈተሽም በጥናቱ የሚመረጡት ተማሪዎች የሚማሯቸውን የመጻፍ ትምህር ይዘቶች ተመርጠዋል፡፡በዚህም መሰረት ከ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማሪያ መጻፍ ውስጥ የሙከራ ትምህርቱ ለስድስት ሳምንታት (ለአስራ ሁለት ክፍለ ጊዜዎች) የተከናወነ ሲሆን በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ስድስት የመጽሀፍ ትምህርት ይዘቶች ተመርጠዋል፡፡ ይዘቶቹ የተመረጡት በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ነው፡፡ይህም የተደረገበት ምክንያት ይዘቶቹ ለውጤት ተኮር የፅህፈት መስተማር ዘዴ አመቺ የሆኑ እና ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡*

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት አይነታዊ እና መጠናዊ የጥናት አይነትን በመከተል ሚከናወነወ ጥናት ነው፡፡ አይነታዊ እና ተናዊ ያስባለውም የሚሰበሰቡት መረጃዎች ቁጥጥራዊ በመሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ አይነታዊ እና መጠናዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡትም በፈተናዎች ነው፡፡ፈተናዎቹ ሁለት ሲሆኑ ከትምህርት በፊት (ቅድመ ፈተና) ከትምህርቱ በኋላ (የድህረ ፈተና) ይሰጣሉ ፡፡ሁለቱም ፈተናዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ የየራሳቸው ዓላማዎች አሏቸው፡፡

ሁለቱም ፈተናዎች ተመሳሳይ ዘትና ቁጥጥር ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚደረግበት ምክንያት የትምህርት አቀራረቡ ከትምህርት በኋላ በተማሪዎቹ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች በመጻፍ ችሎታ ላይያመጣውን መሻሻል ለመገምገም ፈተናዎቹ ይዘቶችም ሆኑ መጠናቸው ተመሳሳይ መሆን ስለሚጠበቅባቸው ነው፡፡

የምርምር ውጤቶች በመረጃ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው መረጃዎቹ ደግሞ በመረጃ መሰብሰብ ዘዴዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው ያለው (2006) ይገጻሉ፡፡ አጥኚው በዚህ ምክንያት ለዚህ ጥናት ሁለት መረጃ መሰብሰብያ ስልቶችን ተጠቅሟል፡፡እነሱም ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ እነዚህ ደግሞ በምርምር ሥራ ውስጥ የሚታወቁ የመረጃ ማሰባሰብያ ስልቶች ናችው፡፡እነዚህን ዘዴዎች አንድ በአንድ በማንሳት ለምን እንደተመረጡ እና ለማን እነደሚቀርቡ ለማብራራት እሞክራለሁ፡፡

### 3.3.1. ፈተና

የዚህ ጥናት ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሁኖ የሚያገለግለው ፈተና ነው፡፡ የተሰጠውም ሁለት ጊዜ ሲሆን ሁለት አላማዎች ይኖሩታል፡፡

### 3.3.2. ቅድመ ትምህርት ፈተና

በመጀመርያ ደረጃ ለተጠኚ ተማሪዎች የሚቀርብላቸው የቅድመ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ይህ ፈተና ተጠኚ ተማሪዎች አስቀድሞ ያላቸውን የጽፈት ዳራዊ ችሎታ ለመለካት በጽፈት ውጤታቸው መሰረት በችሎታ አቻ ወይም ተመጣጣኝ የሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ብሎ ለመመደብ ያገለግላል፡፡ፈተናው የክፍል ደረጃውን መማርያ መጽሀፍ መሰረት ተደርጎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ፈተናው ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት አስተማማኝነቱን ለመጠበቅ የአጥኚውን አማካሪ እና ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን እንዲገመግሙት

ተደርጓል፡፡ ፈተናው ከተገመገመ በኋላ በጥናቱ ከሚሳተፉ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ባላቸው እና ተጠኚ ሁነው ባልተካተቱ ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት ተከናውኗል፡፡የሙከራ ፈተናው በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሞ በአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር አስተማማኝነቱ ታይቷል፡፡በሙከራ ጥናቱ የተገኘ ውጤት ለዋናው ጥናት መሰረት የጣለ ሆኗል፡፡

## 3.3.3. ድህረ ትምህርት ፈተና

ድህረ ትምህርት ፈተናው መሰረት አድርጎ የተዘጋጀው የተሰጠውን ትምህርት (ልምምድ) ነው፡፡አጥኚው ትምህርቱ ከሚጠናቀቅበት ቀን አስቀድሞ በተሰጠው ትምህርት አቀራረብና አተገባበር መሰረት በማድረግ የድህረ ትምህርት ፈተና ጥያቄዎች አዘጋጅቷል፡፡የድህረ ትምህርት ፈተና ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር ተመሳሳይ ሁኖ የሚዘጋጅ ሲሆን የድህረ ትምህርቱ ፈተና አላማ ተደርጎ የተዘጋጀው ተማሪዎች በውጤት ተኮር አቀራረብ ትምህርት ከተማሩ በኋላ ዘዴው በተማሪዎች የመጻፍ ውጤት ላይ ያለውን አስተዋጽዖ ለማወቅ ይረዳል፡፡ፈተናው የክፍል ደረጃውን የመማርያ መጻህፍ ፣የመምህሩን መምርያ መሰረት አድርጎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ይህ በአጥኚው የተዘጋጀው ፈተና እንደ ቅድመ-ትምህርት ፈተና በአማካሪና አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን ከተገመገመ በኋላ በሰጡት አስታየት መሰረት የሚዘጋጅ ነው፡፡

ባጠቃላይ የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ አዘገጃጀት የጥያቄ አወጣጥ መርሆችንና በክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት ያደረገ ነው፡፡

## 3.3. 4 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸው ለሙከራ ቡድኑ እና ለቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁ ከተዘጋጀ በኋላ መጠይቁ በሶስት የአማርኛ መምህራን እና በአማካሪዬ በኩል ተገምግሞ አስተማማኝነቱ ከተረጋገጠ በኋላ በተማሪዎቹ እንዲሞላ የተደረገው በቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቆቹ በተማሪዎቹ እንዲሞሉ የተደረጉበት ምክንያት በቅድመ ትምህርት ተማሪዎች በዘዴው ላይ ከመነሻ የነበራቸውን ፍላጎት ለማወቅ ሲሆን፣በድህረ ትምህርት መጠይቁን እንዲሞሉ የሚደረግበት ምክንያት ደግሞ በተሰጠው አቀራረብ ጽህፈትን ማስተማር የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ነው፡፡ ዓላማው ተማሪዎቹ በውጤት ተኮር ማስተማር ዘዴ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ

አመለካከታቸው ላይ ልዩነት መምጣት አለመምጣቱን ለማወቅ ሙከራ ቡድኑ እና ቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ እና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ ይህም አጥኚው የመጠይቅ ምላሾቹም በፈተናዎቹ ካስመዘገቧቸው ውጤቶች ጋር እየተዛመደ ትንታኔ ለመስጠት ያግዘዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ አደረጃጀት እና አተናተን ዘዴ

ዘዴዎችየዚህን ጥናት አላማ ለማሳካት ተግባር ላይ የዋሉ የመረጃ መ ሰባሰቢያ ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን ከፈተናዎቹ የሚሰበሰቡት መረጃዎችም መጠናዊ እና አይነታዊ መረጃዎች የዚህን ጥናት አላማ ለማሳካት ተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ፈተና ናቸው፡፡በመሆኑም መተንተኛ ዘዴዎቹም መጠናዊ ናቸው፡፡በዚህም መሰረት የጥናቱን አላማዎች ማሳካት የሚችሉት ሁለት መጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡እነሱም ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ (descriptive group statistics) እና ባዕድ የናሙናዎች ተ-ቴስት (independent sampl t-test) ናቸው፡፡እነዚህ የመተንተኛ ዘዴዎች የየራሳቸው ዓላማዎች አሏቸው፡፡

ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት በሁለቱ ቡድን ውስጥ የሚካተቱት ተማሪዎች ትምህርቱን ከመማራቸው በፊት እና ተምረው ከጨረሱ በኋላ በመጻፍ ክሂል ውጤታቸው ላይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡ እንዲሁም በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስትን መጠቀም ያስፈለገው ቡድኖች ከትምህርቱ በኋላ የውጤት ለውጥ አምጥተው ከሆነ ለውጡ ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ተመርምሮበታል፡፡

በሌላ መልኩ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ የመጻፍ ክሂል ፈተና እና ድኅረ የጽሁፍ ፈተና ውጤቶች ተለይተውበታል፡፡በመሆኑም በድኅረ ፈተናው ሂደት ተማሪዎቹ ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቃላት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ከስርዓተ ነጥብ አጻጻፍ እንዲሁም ከአጠቃላይ ድኅረ የመጻፍ ክሂል አንጻር ያስመዘገብካቸው ውጤቶች በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በተካሄደው ቅድመ የናሙና ጥናት እና የናሙና ጥናት የመረጃ ማሰባሰብያ መሳሪያዎቹ (ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ) ያስተማማኝነት እና የትክክለኛነት ደረጃቸው እንደተሻሻለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ በዋናው ጥናት የተገኙ ውጤቶች የሚተነተኑበት እና ማብራሪያ የሚሰጥበት ነው፡፡በዚህ የዋና ጥናት ሂደት የጥናቱ አላማ ላይ በመመስረት የተማሪዎቹ ቅድመ እና ድህረ ፈተና፣ የተማሪዎቹ ቅድመ እና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ከተገኘው የትንታኔ ውጤት በመነሳትም በዝርዝር ማብራሪያ እንዲቀርብባቸው ተደርጓል፡፡

**ዋና ጥናት**

በዚህ ንዑስ ርዕስ የጥናቱ ዋንኛ መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ በመመስረት መረጃዎቹ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡መረጃዎቹ ከመተንተናቸው በፊት ግን የሚተነተንበት ዘዴ ለመወሰን መሟላት የሚኖርባቸው ቅደመ ሁኔታዎቹ ተተንትነዋል፡፡ከትንታኔዎቹም በመነሳትሰ ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡

**4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና**

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ ውጤት ተኮር የመጻፍ  የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽዖ አለውን? የሚል ሲሆን መላምቱ ደግሞ ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር  አስተዋጽኦ  የለውም፡፡ የሚል ነው፡፡ጥያቄውን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሸ መረጃዎች በባእድና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተኗል፡፡

ምዘናው የተከናወነው በርቱእ የጽህፈት ምዘና ዘዴ ነው፡፡ርቱእ የጽፈት ምዘና ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በጻፏቸው ጽሁፎች አማካኝነት መመዘኑ ላይ ያነጣጥራል ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዲህ አይነቱ ምዘና ተማሪዎች መረጃን እዲተነትኑ ፣ እዲያጠቃልሉ፣ በአዲስ መልክ እዲያደራጁና እዲገመግሙ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ተመራጭነት እያገኘ ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ርቱእ የጽፈት ምዘናዎች ከኢርቱእ  የጽፈት ምዘናዎች በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ ስለሚለኩ በብዙ የትምህርት ተቋማት ተመራጭ እየሆኑ መጥተዋ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን ጹሁፍ ችሎታ እንዲያዳብሩ ያበረታታሉ፡፡ ከዚህም በላይ ርቱእ ምዘናዎች እውናዊ (Authentic) በመሆናቸው ጠቃሚ ናቸው፤ ምክንያቱም አብዛኞቹ ተግባራት የገሀዱን አለም የሚወክሉ ናቸው፡፡ ርቱእ የጽህፈት ምዘናዎች ሁሉም የጽህፈት አለባዉያን አዋህደው የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም በርቱእ የጽህፈት ምዘና አማካኝነት

አንድ ጸሀፊ ምን ያህል ጥሩ ጻፊ ወይም በጽሁፍ አማካኝነት ምን ሊያከናውን እነደሚችል መግለጽ ይቻላል (Weir, 1993) ፡፡

የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከሙከራ በፊት ያላቸው የመጻፍ ክሂል ችሎታ ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር በባእድና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ የተገኘው ውጤትም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.1፡- የተተኳሪ ቡድኖች ቅድመ ፈተና ውጤት ንጽጽር /በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/**

| ምድብ | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ T | የነጻነት ደ (DF) | የጉልህነት ውጤት (sig |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 30 | 53.77 | 10.23412 | -1.539 | 60 | 0.024 |
| የቁጥጥር ቡድን | 30 | 50.25 | 7.78514 | | | |

ከላይ በሰንጠረዡ ያለው መረጃ የሚያሳየው የቅድመ ፈተናውን የተፈተኑ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት (53.7778) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት (50.2571) በ (3.5207) የበለጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት (10.23412) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት (7.78514) በ (2.44898) ልዩነት አምጥቷል፡፡

ከቀረበው ትንተና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት እንደበለጠ ለማየት ተችሏል፡፡

በመካከላቸው ያለው የጉልህነት ደረጃ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው በ 60 የነጻነት ደረጃ ቲ (-1.539) =2.00 ፣ የጉልህነት ውጤት (sig=0.024) ከ0.05 በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካዮች መካከል የጎላ ልዩት አለመኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተተኳሪ ቡድኖች መካከል ተቀራራቢ የመጻፍ ክሂል ችሎታ መኖሩን ስለሚያሳይ ሙከራው በቡድኖቹ ላይ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለስድስት ሳምንታት ያክል እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ቡድኖቹ ያመጡትን ለውጥ ለመመርመር ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፣ ውጤቱ በባእድና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ ተሰልቷል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም የተገኘውን ውጤት አሳይቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.2፡- የተተኳሪ ቡድኖች ድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት ንጽጽር/ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት/**

| ምድብ | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ T | የነጻነትደረጃ (DF) | የጉልህነት ውጤት (sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 30 | 60.092 | 15.3754 | -2.799 | 60 | 0.000 |
| የቁጥጥር ቡድን | 30 | 52.000 | 6.6421 | | | |

ከድህረ ትምህርቱ የመጻፍ ክሂል ፈተና መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (60.0926) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (52.0000) ልዩነቱ በ (8.0926) በልጦ ተሰልቷል፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ያስመዘገቡት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ በአማካይ ያለው ልዩነት ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት ውጤት (15.37545) ፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና መደበኛ ልይይት ውጤት (6.64211) በ (8.733339) ልዩነት አሳይቷል፡፡

በመሆኑም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሲታይም፣ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት በ60 የነጻነት ደረጃ ቲ (-2.799) =2.00 ፣ የጉልህነት ውጤት (sig. = 0.000) ከ0.05 በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካዮች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ከላይ ባለው ሰንጠረዥ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤቱ ከፍ ብሎ ስለታየ በቡድኖቹ መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ቡድን በቅድመና በድህረ ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት በተናጥል በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ማነጻጸር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመና በድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ያስመዘገቧቸው አማካዮች ሲነጻጸሩ የተገኘው ውጤት ስሌት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.3፡- የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር**

| ፈተና | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 30 | 53.7778 | 10.23412 | -3.706 | 26 | 0.001 |
| ድህረ ፈተና | 30 | 60.0926 | 15.37545 | | | |

ከላይ ባለው ሰንጠረዥ እንደሚታየው የሙከራ ቡድኑ ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (60.0926) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (53.7778) በ6.3138 በልጦ ይታያል፡፡ የመደበኛ ልይይት ውጤት እንደሚያሳየውም የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (15.37545) ከቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (10.23412) በ5.14133 ልዩነት አሳይቷል፡፡

በመሆኑም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሲታይም ፣ የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው በ26 የነጻነት ደረጃ ቲ (-3.706) = 2.06 ፣ የጉልህነት ውጤት (sig. = 0.001) ከ0.05 በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡

የጉልህ ልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ ፣ (Cohen's d= 0.71315) መጥቷል፡፡ ይህ መካከለኛ ዝምድና ጥንካሬ ደረጃን የሚያሳይ ነው፡፡ የዝምድና ጥንካሬ ደረጃ የባለ ሁለት ጫፍ የsig. ዋጋ ከ0.05 በታች ከሆነ የሚሰላ ነው፡፡ የጉልህነት ውጤቱ ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ሲያመለክት ፣ Cohen's d (1988) ደግሞ ከsig. ዋጋው በመነሳት የጉልህነት ደረጃውን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት ከ0 - 0.2 = ደካማ ፣ ከ0.21-0.5= መጠነኛ ፣ ከ0.51- 1=መካከለኛ እና ከ1 በላይ ጠንካራ የጉልህነት ደረጃን ያመለክታል፡፡

የትንተና ወጤቱም እንደሚያሳየው የዝምድና ጥንካሬው መካከለኛ ቢሆንም ከድህረና ቅድመ የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው ያሳል፡፡ ይህ ልዩነት የመጣው

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን በመማራቸው እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎች ያስመዘገቧቸው አማካዮች ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለመቻላቸውን ለመፈተሽ ውጤቱ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ ተሰልቷል፡፡ ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥም የተገኘውን ውጤት ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.4፡- የቁጥጥር ቡድኑ ቀድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር**

| ፈተና | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 30 | 50.2571 | 7.78514 | -2.234 | 34 | 0.032 |
| ድህረ ፈተና | 30 | 52.0000 | 6.64211 | | | |

ከላይ እንደሚታየው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (52.0000) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (50.2571) በ 1.7429 በልጦ ይታያል፡፡ የመደበኛ ልይይት ውጤት እነደሚያሳየውም የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (6.64211) ከቅድመ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (7.78514) በ 1.14303 ልዩነት አሳይቷል፡፡

በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሲታይም ፣ ቅድመ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው በ34 የነጻነት ደረጃ ቲ- (-2.234) = 2.04 የጉልህነት ውጤት 0.032 ከመቁረጫው ነጥብ 0.05 በታች መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከላይ እንደሚታየው በሙከራ ቡድኑ ከድህረ የመጻፍ ክሂል ውጤት አንጻር ጉልህ ልዩነት ሲታይ በቁጥጥር ቡድኑ ግን ጉልህ ልዩነት አልታየም፡፡ የውጤቱ ልዩነትም ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ በመተግበሩ ምክንያት የመጣ መሆኑን ሊጠቁም ይችላል፡፡

ተጠኚው በተለመደው አቀራረብ መማራቸው የጽህፈት ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሌለው የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መልክ ሲታይ የሙከራ ቡድን የጽህፈት ትምህርት የጽህፈት ውጤት(25.67) በትምህርት የጽህፈት ችሎታ በአማካይ ውጤት(19.07)

ጋር ሲነጻጸር በአራት ልቆ ይገኛል፡፡ ልዩነቱ የጎላ መሆኑ ብሎም ብልጫ እንዳለው የሚያሳይ ሆኗል፡፡ ስለዚህም የሙከራ ቡድኑ ከትምህርት በፊት እና ከትምህርት በኋላ የጽሁፍ ፈተና ውጤት ልዩነት አሳይቷል፡፡ ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ ውጤት የምንረዳው በልይይታዊ ማስተማር ዘዴ ጽህፈት ትምህርት መከታተል በጽህፈት ችሎታ ቀድሞ ከነበረው የተሸለ ለውጥ ማስመዝገብ እንደቻለ ነው፡፡ በሁለቱም አማካዮች መካከል ልዩነት ያመጣው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በተሸለ አዋጭ በሆነ መንገድ የጽህፈት ትምህርቱን መከታተል በመቻሉ ነው፡፡ በዚህም በጥናቱ መግብያ ላይ ቀርቦ የነበረው መላምት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ ማለት በውጤት ተኮር ማስተማር ዘዴ እና በተለመደው ማስተማርያ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎች የጽህፈት ችሎታ ላይ ያለው አስተዋጽኦ ልዩነት አይኖረውም (የለም ) የሚለው መላምት ውድቅ ሆኗል፡፡ በውጤት ተኮር ጽህፈትን ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጾ አለው የሚለው መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በጥናቱ ሊመለስ የተፈለገው ሁለተኛ መሰረታዊ መላምት ውጤት ተኮር ጽህፈትን ማስተማር ዘዴ እና በተለመደው የማስተማር ዘዴ ጽህፈትን ማስተማር በተማሪዎች የመጻፍ  ችሎታ ላይ አስተዋጽኦ የለውም የሚለው ነው፡፡ ይህንን መላምት ለመመለስ ተግባራዊ የተደረገው የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገው በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ጽህፈት ትምህርት ደረጃ ነው፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ከልምምዱ በፊት ያላቸውን የጽህፈት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መረጃ መለየት ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት አስፈላጊ ነው፡፡በዚህ መሰረት በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና በመሆኑ በተሞላው የጽሁፍ መጠይቅ የሙከራ ቡድን እና የቁጥጥር ቡድንኑ ቅድመ የጽሁፍ መጠይቅ የመጻፍ ችሎታ በንጽጽር ሰንጠረዥ 4.4 የሚመለከቱ የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር በድኑ ድህረ የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ንጽጽር እንደሚከተለው በሰንጸረዥ 4.5 ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሰረት የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ እና ድህረ የመጻፍ ፍላጎት እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ የመጻፍ ችሎታ ንጽጽር በሰንጠረዥ 4.6 ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.5 የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ የመጻፍ ችሎታ ንጽጽር(በባእድ ናሙና ቲ ቴስት)**

| የሙከራ ቡድን | | | የቁጥጥር ቡድን | | | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህ ደረጃ ባለሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ናሙና | አማካይ ልይይት | መደበኛ ልይይት | | | |
| 30 | 28.4 | 2.41 | 30 | 27.6 | 2.18 | 1.58 | 78 | 0.123 |

ሰንጠረዥ 4.5 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ የመማር ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት 27.6 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ጽሁፍ የመማር ፍላጎት ምላሽ የተገኘው አማካይ ውጤት ደግሞ 28.4 ነው፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ሆነ የሙከራ ቡድኑ ከትምህርቱ በፊት ተመሳሳይ ጥህፈትን የመማር ችሎታ እንዲኖራቸው ያሳያል፡፡

በሰንጠረዥ 4.5 የተመዘገቡት የመደበኛ ውጤቶች በአማካይ ውጤት ያላቸው ርቀት የተቀራረበ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የተገኛው የቲ ዋጋ ( 1.56) ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ ( 2.000) ያነሰ በመሆኑ ተጠኚ ተማሪዎች ያላቸው ቅድመ ትምህርት ጽህፈትን የመማር ችሎታቸው ተቀራራቢ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ሌላው በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ የድህረ ጽሁፍ ችሎታ መጠይቅ ነው፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛ መንገድ የሙከራ ቡድኑን ደግሞ አጥኚው ባዘጋጀው በውጤት ተኮር ማስተማርያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ከሞሉት ጽፈትን የመማር ፍላጎት አንጻር በሰንጠረዥ 4.6 ተነጻጽሮ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.6 የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረ ጽህፈት የመማር ፍላጎት ንጽጽር በባእድ ናሙና ቲ ቴስት**

| የሙከራ ቡድን | | | የቁጥጥር ቡድን | | | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህ ደረጃ ባለሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ናሙና | አማካይ ልይይት | መደበኛ ልይይት | | | |
| 30 | 35 | 3.45 | 30 | 28.3 | 1.91 | 10.10 | 78 | 0.001 |

ሰንጠረዥ 4.6 እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ የመማር ችሎታ ውጤት 35 ከቁጥጥር ቡድኑ የመማር ችሎታ ውጤት (28.3) ብልጫ አሳይቷል፡፡ በመደበኛ ልይይት የቁጥጥር ቡድን መደበኛ ልይይት ( 1.91) ከሙከራ ቡድን መደበኛ ልይይት (3.37) ያላነሰ መሆኑን ከሰንጠረዥ 4.6 እንደተመለከተው በሙከራ ቡድኑ እና በቁጥጥር ቡድኑ የመማር ችሎታ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት በእስታእስቲክ ጉልህ መሆኑን በማረጋገጥ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሁኗል፡፡

ሰንጠረዥ 4.6 እንደተገለጸው በ78 የነጻነት ደረጃ የP ዋጋ 0.000 (ቲ= 10.10) 2P<0.05 ሲሆን P>0.05፤ የቲ ዋጋ (10.10) ከቲ- sri(2.000) ጉልህ ሆኖ መገኘቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በሁለቱ አማካዮች መካከል ልዩነት የሚመጣው የሙከራ ቡድኑ በውጤት ተኮር ጽህፈትን የማስተማር ዘዴ መማራቸው ከተለመደው አቀራረብ በላይ የተማሪዎችን የጽህህፈት ችሎታ ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ይህን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ቅድመ የጽህፈት መጠይቅ እና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ በማነጻጸር ሰንጠረዥ 4.7 መመልከት ይቻላል፡፡

ሰንጠረዥ 4.7 የቡድኖቹ ቅድመ እና የድህረ ጽህፈትን የመማር ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ተናጥላዊ ንጽጽር (በዳግም ልኬት ናሙና ቲ ቴስት )

| የተጠ ቡድ | የጽሁፍ መጠይቅ | የጽሁፍ መጠይቅ | | | ተቀንሶ የተገኘ አማካይ ውጤት | ተቀንሶ የተገኘ መደበኛ አማካይ ውጤት | የነጻነት ደረጃ (df) | የተሰላ የ ዋጋ t-test | የሁለተኛ ደረጃየባለ ሁለት ጫፍ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | | | |
| የቁጥጥር ቡድኑ | ቅድመ ትምህርት | 30 | 27.62 | 2.18 | 07 | 0.27 | 39 | 1.87 | 0.92 | የለም |
| | ድህረ ትምህርት | | 28.3 | 1.91 | | | | | | |
| የሙከራ ቡድን | ቅድመ ትምህርት | 30 | 28.4 | 2.41 | 6.6 | 1.33 | 39 | 10.96 | 0.001 | አለ |
| | ድህረ ትምህርት | | 35 | 3.74 | | | | | | |

- የቁጥጥር ቡድኑ፡- /P>0.05/ሲሆን

- የሙከራ ቡድን፡- /P<0.05/

ሰንጠረዥ 4.7 እንደሚያመለክተው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 22.9 ጋር ሲነጻጸር በልጦ የታየው 0.7 ብቻ ነው፡፡ ይኸመወ ልዩነት ጉልህነት  እንዳለው እና እንደሌለው በዳግም ውጤት ናሙና ቴስት (repeated measure sample t-test) ተፈቷል፡፡ በፍተሻውም የ”t” ስሌት ዋጋ /tab/ 1.87 ሲሆን በ0.05 የጉልህ ደረጃ በ39 የነጻነት ደረጃ ባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ “t” ሰንጠረዥ ዋጋ/tort/ 2.021 ሆኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም መሰረት የ”t” ስሌት ዋጋ /1.87/ ከሰንጠረዥ የ “t” ዋጋ ሲነጻጸር አንሶ ተገኝቷል፡፡ይህም ቡድን በድህረ ትምህርት እና ከቅድመ ጽህፈት ትምህርት የጽህፈት ችሎታ ውጤት ጉልህ ልዩነት አለመታየቱ ሊያመለክት የችላል፡፡ ይህ የቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች መማራቸው የጽህፈት ችሎታ የመማር ፍላጎታቸው በማሻሻል ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሌለው የሚያሳይ ነው፡

በሌላ መልኩ ሲታይ የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የጽህፈት ችሎታ መጠየቅ አማካይ ውጤት -35- ከቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት/27.6/ ጋር ሲነጻጸር በ7.4 ልቆ ይታያል፡፡ ልዩነቱም የጎላ መሆኑ ብሎም ብልጫ እንዳለው የሚያሳይነው፡፡ ስለዚህም የሙከራ ቡድኑ ከትምህርት ፊት እና ከትምህርት በኋላ የጽህፈት ችሎታ ልዩነት ሳይቷል፡፡ በሙከራ ቡድኑ ውጤት ተኮር የማስተማርያ ዘዴ የጽህፈት ትምህርት መማራቸው የመጻፍ ችሎታቸው በመሻሻሉ ተማሪዎቹ ቀድሞ ከነበራቸው ችሎታ የተሸለ ግንዛቤ አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡

በሁለቱ አማካዮች መካከል ልዩነት ያመጣው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በላይ የተማሪዎችን የጽፈት ችሎታ በማጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል ወደሚል መደምደምያ ያደርሳል፡፡ አይታይም በሚል የቀረበው የጥናቱ መላምት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ ማለት በውጤት ተኮር ማስተማርያ ዘዴና በተለመደው ማስተማር ዘዴ መጻፍን ማስተማር በተማሪዎች የጽህፈት መማር ችሎታ ላይ ልዩነት አይኖረውም( የለውም) የሚለው መላምት ውድቅ ይሆንና ተለዋጩ መላምት (በውጤት ተኮር እና በተለመደው ጽህፈትን የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ትምህርት ውጤት ላይ ልዩነት አለው፡፡) የሚለው መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡በአጠቃላይ የዚህ ውጤት እንደሚያመለክተው በውጤት ተኮር ማስተማርያ የቀረበው ዘዴ የመጻፍ ትምህርት ችሎታ ለማሻሻል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

በቅድመ ትምህርት ፈታና እና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በእስታቲስቲክስ ጉልህ ልነት ($p<0.05$) ታይቷል፡፡ በተጨማሪም በውጤት ተኮራ ማሰተማርያ ዘዴ እና በተለምዶአዊ ማስተማርያ ዘዴ ማስተማር የጽህፈትን ችሎታ ከማሳደጉ አንጻር ልዩነት አለ፡፡ በውጤት ተኮር ማስተማርያ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት ችሎታ አማካይ ውጤታቸው በእስታቲስቲክስ ጉልህ ($p<0.05$) ሁኖ ሲታይ በተለመደው የማስተማርያ ዘዴ ጽህፈትን የተማሩ ተማሪዎች የጽህፈት ፈተና አማካይ ውጤታቸው በእስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p>0.05$) ሆኖ አልታየም፡፡ ይህም ውጤት ተኮር ማሰተማር ዘዴ ከተለምዶአዊ ማስተማር ዘዴ በላይ የጽህፈት ትህርት ችሎታን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በውጤት ተኮር ማስተማርያ ዘዴ እና በተለምዶአዊ ማስተማርያ ዘዴ ተማሪዎች ጽህፈትን በመማረ ችሎታቸው ላይ ልዩነት አለ፡፡ በውጤት ተኮር ማስተማርያ ዘዴ ጽህፈትን የመማር ችሎታ ውጤት አማካይ ውጤት መካከል በእስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p< 0.05$) ታይቷል ነገር ግን በተለመደው ማስተማርያ ዘዴ ተማሪዎችን የጽህፈት ትምህርት ውጤት ለማሻሻል

አማካይ ውጤት መካከል በእስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት($p>0.05$) ሆኖ አልታየም፡፡ውጤት ተኮር የማስተማርያ

## 4.2.የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትኩረት ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህ አላማ በአቅጣጫ ጠቋሚ መላምት የተገለጸ ሲሆን የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ እና መላምቶችን ለመፈተሽ በቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን ለማረጋገጥ የተሰበሰቡት መረጃዎች ሁለቱ ቡድኖች በቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ያስመዘገቧቸው ውጤቶች በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት እያንዳንዱን ቡድን በቅድመና ድህረ የመጻፍ ክሂል ያስመዘገቧቸው ውጤቶች በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና እንዲሰላ ተደርጓል፡፡

በጥናቱ ውጤት ትንተና በመጀመሪያ የተፈተሸው የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የቅድመ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም ቅድመ የመጻፍ ክሂል በሙከራና በቁጥጥር ቡዱኖቹ መካካል ጉልህ ልዩነት እንዳልታየ የተገኘው ውጤት አመልክቷል፡፡

በትንተናዉ መሰረት የቁጥጥር ቡድን ተጠኚዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት ከሙከራ ቡድን ተጠኚዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት 3.5207 ብቻ እንደበለጠ ተረጋግጧል፡፡ መረጃዉ በባእድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ዉጤቱ (ቲ=-1.539, የነጻነት ደረጃ= 60, የጉልህነት ደረጃ= 0.024) አሳይቷል፡፡ ይህም ማለት በ60 የነጻነት ደረጃ የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች የባለ ሁለት ጫፍ ልዩነት የጉልህነት ደረጃ (P value)= ከ$p<2.44898$ የበለጠ ነዉ፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ዉጤት ልዩነት አለ ለማለት የ"p" ዋጋ ከ0.05 ማነስ ነበረበት፡፡ በዚህ በባእድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ስሌት መሰረት ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች ከመማራቸዉ በፊት የመጻፍ ክሂል ችሎታቸዉ ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸዉ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ ዉጤት መረዳት የሚቻለዉ ከሙከራ በፊት በሁለቱም ቡድኖች የተመዘገበዉ የጉልህነት ዉጤት ከ0.05 በላይ በመሆኑ ተቀራራቢ የመጻፍ ክሂል ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ያሳያል፡፡ የተገኘዉ ዉጤትም በሁለቱ ቡድኖች ጥናቱን ማካሄድ እንደሚቻል ሊያመለክት ችሏል፡፡

ከቅድመ ፈተና ከተገኘዉ ዉጤት በመነሳት ለስድስት ሳምንታት ጥናቱ በከፊል ሙከራዊ ጥናት ዘዴ ተካሂዶ ሁለቱ ቡድኖች ድህረ የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በዚህም ሂደት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ዉጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ የሙከራ ቡድኑ 30 ተጠኚዎች ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂል የተደገፈ ትምህርት በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ከቀረቡት ምንባቦች መካከል የተመረጡትን የመጻፍ ክሂል መልመጃዎቻቸዉ ጋር በመዉሰድ ለስድስት ሳምንታት በየተመደቡበት ክፍል እንዲማሩ ተደርጎ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ 30 ተጠኚዎች በተለመደዉ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ከምንባቡ የወጣ አንድ ጥያቄ ፈተና ቀረበ፡፡

በድህረ ትምህርት የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት አጠቃላይ ድምር(60.0926) ከቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት አጠቃላይ ድምር(52.0000) በ8.0926 ማርክ ብልጫ መሳየቱ፣ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት(60.0926) ከቁጥጥር ቡድኑ ተጠኚዎች ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት (52.0000) በ8.0926 የአማካይ ዉጤት ብልጫ ማስመዝገባቸዉ ታዉቋል፡፡

መረጃዉ በጥንድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ዉጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ዉጤቱ (ቲ-= -2.799,df=60,p=0.001) መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በ60 የነጻነት ደረጃ የጉልህነት ደረጃ =0.001 ከp<0.05 ያነሰ ነዉ፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ዉጤት ልዩነት መኖሩን የ”p” ዋጋ ከ 0.05 አንሶ መገኘቱ ጠቋሚ ነዉ፡፡ ይህም የሚጠቁመዉ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ ያለዉ መሆኑ እና የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ነዉ፡፡ ውጤቱም እነደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡

ከተገኘው ውጤት በመነሳት ጥናቱ ካስቀመጣቸው መላምቶች “ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽዖ አለው” የሚለው አቅጣጫ ጠቋሚ መላምት ተቀባይነት አግኝቶ “ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽዖ የለውም” የሚለው አቅጣጫ የለሽ መላምት ውድቅ ሆኗል፡፡

ስለዚህ ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ከተለመደዉ መጻፍን ከማስተማሪያ ዘዴ ቡድን ለቡድን ሲወዳደር ጉልህ ልዩነት ባያሳይም እያንዳንዳቸዉ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማነታቸው በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ በውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማር ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡

# ምእራፍ አምስት

ማጠቃለያ ፣መደምደሚያ ፣ሚየመፍትሄ ሀሳቦች እና ወደፊት ሊጠኑ የሚገባቸው መሰረታዊ ነጥቦች::

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ማጠቃለያ፣መደምደሚያ፣የመፍትሄ ሃሳቦችና ወደፊት ሊጠኑ ሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡በመጀመሪያ ማጠቃለያ በሚለው ንዑስ ስር ከጥናቱ ዋና አላማዎች፣ጥያቄዎች እና መላምቶች በመነሳት፣ጥናቱ ዘዴ እና የተገኙ ውጤቶችን ለማሳየት ተችሏል፡፡ በሁለተኛው ንዑስ ርዕስ ስር በጥናቱ ከተገኙት ውጤቶች ላይ በመመስረት የተሰነዘሩ ማብራሪያዎች ተጠቃለው ቀርበው ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡በመፍትሄ ሀሳቦች ስር ደግሞ ከጥናቱ አጠቃላይ ግኝት በመነሳት ከውጤት ተኮር የጽህፈጽ ማስተማር ዘዴ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

## 5.1ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉን አስተዋጽዖ መለየት ነዉ፡፡ ጥናቱ ምላሽ ሊሰጥበት ያነሳዉ መሰረታዊ ጥያቄ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽዖ አለዉን? የሚልነዉ፡፡

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በቡኖ በደሌ ዞን በበደሌ ከተማ በእንግቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዉ፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ 2016 ዓ.ም ትምህርታቸዉን የሚከታተሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸዉ፡፡በክፍል ደረጃዉ ስድስት የመማሪያ ክፍሎች ዉስጥ ተመድበዉ የሚማሩ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ተማሪዎች የሚማሩ ሲሆን ለጥናቱ የሚሆን ናሙና አስፈላጊ በመሆኑ ተራ የእጣ ንሞና ዘዴን በመጠቀም የምድብ 10-“B” እና 10- ‘’F’’ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የተመረጡ ሲሆን በእነዚህ ክፍሎች የሚማሩ 60 ተማሪዎች በሙሉ በጠቅላይ ንሞና የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ነገር ግን ሰላሳ አራቱ ተማሪዎች ትምህርቱን አቋርጠዋል፡፡ የተቀሩት 60 ተማሪዎች ትምህርቱን በመከታተል ለጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ከሁለቱ ምድቦች በተራ የእጣ ንሞና ምድብ “B” የሙከራ ቡድን ሲሆን ምድብ “F” ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ሆነዋል፡፡የጥናቱን መሰረታዊ መላምት ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ቅድመ እና ድህረ ፈተና ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች ያላቸዉን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለመለካት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁት ቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከመቅረባቸዉ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አይተዉታል፡፡ ከዚያ ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

በዚህ ጥናት ከፈተና በተጨማሪ የጽሁፍ  መጠይቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስራ ላይ ውሏል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ እንደ ደጋፊ የመረጃ መስሰብያነት ተጠቅመን ተማሪዎች በሁለቱ አቀራረብ (በውጤት ተኮር ማስተማር ዘዴ እና በተለምዶአዊ ማስተማር ዘዴ) የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸውን አስተዋጽኦ ለመለካት ልዩነት መኖሩን አለመኖሩን ለማወቅ የጽሁፍ መጠይቁ ሀያስድስት ጥያቄዎች የተካተቱበት ሲሆን የጽህፈት ችሎታዎች ለማሳካት የተጠቀመበትን ለጥናቱ በሚመች መልኩ በማሻሻል በአጥኚው ተዘጋጅቷል፡፡

በመቀጠልም እንደፈተናው አዘገጃጀት መሰረት በመታየት እና በመፈተሽ ተማሪዎቹ ለጽህፈት ችሎታ ያላቸውን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር እንዲሳካ  ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውተፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዉ ከተመዘገቡ በኋላ የሁለቱን ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማነጻጸር በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲተነተን እያንዳንዱ ቡድን ከሙከራ በኋላ ያመጣዉን ለዉጥ ለመለየት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ ውጤት ተኮር ጽህፈትን የማስተማሪያ ዘዴ ከተለመደዉ መጻፍን ከማስተማሪያ ዘዴ ቡድን ለቡድን ሲወዳደር ጉልህ ልዩነት ባይኖረዉም እያንዳንዳቸዉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ዉጤታማነታቸዉ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ በውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ጉልህ ልዩነት ስላመጡ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር አስተዋጽዖ እንዳለው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ዉጤት ውጤት ተኮር የመጻፍ የማሰተማሪያ ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት ቢተገበር የተማሪዎችን የመጻፍ  ችሎታ ለማሳደግ አስተዋጽዖ ሊኖረው እንደሚችል አመልክቷል፡፡ሏል፡፣

## 5.2 መደምደሚያ

ቀደም ሲል ከተሰጠው የጥናቱ ዓላማ በመነሳት ፣ከተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት እና በትንተናው ሂደት የተገኙ ውጤቶች ላይ በመመስረት የሚከተሉ መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ በመካከለኛ ክፍል ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች (በአስረኛ ክፍል ናሙናነት) ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማር ዘዴ በየደረጃው ተከፋፍሎ ሲተገበር ፣ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በመሆኑም

- ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ ከመጻፋቸው በፊት ለመጻፍ እንዲያስቡ፣እንዲያሰላስሉ ከዚያም የተረዱትን ሃሳብ የቋንቋውን መዋቅር ጠብቀው ማለትም የቃላት፣የሀረጋት ፣የአረፍተ ነገር አመሰራረት ፣የአንቀጽ አጻጻፍ እና የስርአተ ነጥብ አገባብ በጽሁፋቸው ውስጥ እንዲያነሱ ከማድረግ አንጻር ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማርያ ዘዴ አስተዋጽዖው ከፍተኛ ነው፡፡

ከጥናቱ ዉጤትና ማብራሪያ ማየት እደንሚቻለዉ ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ ከተለመደዉ መጻፍን ከማስተማሪያ ዘዴ ቡድን ለቡድን ሲነጻጸሩ ጉልህ ልዩነት ባይኖረዉም እያንዳንዳቸዉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ዉጤታማነታቸዉ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት እና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ በውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል ፡፡ ስለዚህ ውጤት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽዖ አለዉ ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

## 5.3 አስያተያየት

የመጻፍ ክሂል አፍልቆትን የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎች ከአእምሮአቸው እያፈለቁ የተለያዩ ጽሁፎችን መጻፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ይህ ደግሞ ውጤታማነቱ ለረጋገጥ የሚችለው ተማሪዎቹን አሳታፊ የሚያደርጉ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባር ላይ በማዋል ነው፡፡በዚህም ሂደት ሥራ ላይ የዋለው የማስተማሪያ ዘዴ ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ ከመጻፍ ችሎታ እና ውጤታማነት አንጻር ተፈትሾ የተገኘው ውጤት አውንታዊ ነው፡፡

ከጥናቱ ዉጤት በመነሳት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ የሚከተሉት የመፍትሂ ሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

## 5.3 አስተያየት

- ሱፐርቫይዘሮች የውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማር ዘዴን ለመምህራን እና ለተማሪዎች ስልጠና እንዲሰጥ የማመቻቸት ስራ ቢያከናውኑ የተሻለ ይሆናል፡፡
- መምህራን ውጤት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ከመጻፍ ክሂል ችሎታጋር ያለዉን ቀጥተኛ ግንኙነት ተገንዝበዉ የመማር ማስተማሩን ሂደት በዚህ ዘዴ ቢተገብሩ የሚመለከታቸዉ አካላትም ክትትልና ድጋፍ ቢያደርጉ፡፡
- ውጤት ተኮር የጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር አስተዋጽዖ እዳለዉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ የሚዘጋጁ ተግባራት ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴን ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንዲካተቱ የበለጠ ትኩረት ቢደረግባቸዉ፡፡
- በዚህ የጥናት ዉጤት ላይ በመመስረት ከውጤት ተኮር  የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ በተጨማሪ በሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ መምህራንም ሆኑ ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ጥናት ቢያካሂዱ፤ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሀና ታምራት፡፡(2003)፡፡ በሆሳህና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ጽህፈት ክሂል ኮርስ የአቀራረብና የአተገባበር ፍተሻ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲጊሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

መላኩ ባይለየኝ (2013) ሂደት ተኮር መጻፍ ክሂል አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለዉ ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡(ያልታተመ)

መስታወት ተስፋዬ፡፡(2014)ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር እና ተነሳሽነት ለመፍጠር ያለው ሚና (በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን በፈቱ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)፡፡በጅማ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብዕ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ቋነቋ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለአርት ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡(ያልታተመ)፡፡

ማረው አለሙ፡፡ (2005)፡፡ በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡ ሁለተኛ እትም አዲስ አበባ ማተሚያ ድርጅት፡፡ አ-ኩራዝአሳታሚ ድርጅት

ማሬ አሰፋ፡፡ (2011)፡፡ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ በዘጠነኛ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ከፊል ሙከራዊ ጥናት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ

በላይነህ አየነዉ፡፡ (2000)፡፡ ሂደታዊ የአጻጻፍ ብልሃት ለአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት ያለዉ ሚና፡፡ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ተመስገን ፈቀደ፡፡ (2001)፡የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፍት ክሂል ማስትማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ብለሃት ተዛምዶ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ቱሉ ንጉሱ (2014) የኦሮምኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሚቸዉ ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና፡ (በጮራ ቦተር ወረዳ ሶስት

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)

አለምነሽአሰፋ (2011) ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴን በመጠቀም ጽህፍትን ማስተማር የጽህፈትን ክሂል በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና (በደቡብ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሀደሮ ከተማ አስድደር ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማዎች ተተኳሪነት ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

አማረ ተሾመ፡፡ (2010)፡፡ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት አስተዋጽኦ ለማሻሻል ያለው ተጽእኖ፡፡ ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡አዲስአበባዩኒቨርሲ

አንለይ አዳነ፡፡ (2000)፡፡ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የጽህፈ ክሂል ትምህርት ማስተማር ስነ ዘዴዎች አተገባበር፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፡፡(ያልታተመ)፡፡

አድማሱ አክሊሉና ደምሴ ማንያሎት፡፡ (1982)፡፡ ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው አዲስአበባ፤ ዩኒቨርሲቲ፡፡

እስከዳር ገበየሁ፡፡ (2011)፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው

ስህተቶች ትንተና በዘጠነኛ ክፍልአፈ- ፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጎንደርዩኒቨርሲቲ፡፡

የአምላክስራ ህይወት፡፡ (2008)፡፡ የአማርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሟቸው ሰህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና ፤ በአዲስ አበባ ከተማ

በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡ ለተግባራዊ ስነልን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ድጊሪ ማሟያየ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ያለው እዳወቀ (2011)፣ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር ፣ሶስተኛ እትም ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ደረጀ ገብሬ እና ግርማ፡፡ (1999)፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድርሰት የመጻፍ ብለሃት ተዛምዶ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

Ashraf,A.(2016). ESL learners' Writing skills: Problemse,factors,and suggestions. of Education and social sciences, 4(2):1
shttp://dx.doi.org/10.20547/jess0421604201

Atkinson,D.(2003)"L2 writing in the post process era,Introduction on'' Jornal of seconde Language writing .123-15.Byren, (1988).Teaching writing skills.Longman Group up Limited.(1988).

Brakus,P(2003). "A /process/gener approach toteaching writing asynthesis of bnnapproach in aletter writing course nonnative English speaking administrative perosonne" Unpuplished dissertation, universityof surrey.m.a, Allynand Bacon.

Brown (2001).Teaching by principle an interactive approach to Language Pedagogy (2nd ed)New york:Addison wesiy.

Byrne,D. (1988). Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group Ltd.

Byrne,(1997) . Teaching Writing Skills. London: Longman Group Ltd.

Clork,I. ( 2003). Concept in Composition theory Cend Practice in the teaching writing lawrecheah, Laboum assocated pliblisher, mchiwah New,

Jersy; londen.

Ellis, R. (1994) e study of second language acquisition: oxford: oxford university
File:///c:/users/hp/desktop/amharic%20thesis/unit_4.pdfhttps://happynumbers.com/blog/list-of-teaching-methodologies-primary-school/

Harmer, J. (1991).The practice of English language teaching. London: London group Ltd

Hedge, T. (1991). Writing. Oxford. Oxford university.

Kroll,B. (1990) .Second language writing Research in sight for the Class room Cambridge, Cambridge University Press.

Nunan, D. (1989). Designing tasks foer the communicative classroom. Cambrigde: cambrigde university press. International journal for infonomics(IJI), volume 13, issue 2, 2020)፡፡

Raimis, A. (1983). Techniques in the Teaching Writing. Oxford: Oxford University press.

Richards,J.C.(1974). Error Analysis Perspectives on Second Language Acquisition. London and Newyork: Longman Group Ltd.

Urevdu, A.A. (1985:22). Curriculum studies

Silva,T. (1993). Towards understanding writing. The ESL research and its implication. Joumal of second language writing: 2 p657-677

# አባሪ-1

## ለዋናው ጥናቱ ለቅድመ ትምህርት የቀረበ የጽሁፍ ፈተና

የዚህ የጽሁፍ ፈተና ዋና አላማ የአሰስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡እናም የዚህን ጥናት አላማ ማሳካት የሚቻለው እናንተ የምትጠየቁትን ጥያቄ በትክክል መመለስ ስትችሉ ብቻ ነው፡፡በመሆኑም ቀጥሎ የቀረበውን ጥያቄ በትክክል መልሱ፡፡የፈተናው ውጤትም በተመራማሪዎ ብቻ በሚስጥር ይያዛል፡፡ለምታደርጉት ትብብርም አጥኚው ልባዊ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ለናሙና ጥናቱ እና ለዋና ጥናቱ የቀረበ ቅድመ ፈተና

ምድብ---------------

ጊዜያዊ የመለያ ኮድ ቁጥር------------

ማሳሰቢያ

ሀ.ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ለ.የምትጽፊው (ፊ) ጊዜያዊ የመለያ ኮድ ቁጡሩን ብቻ ነው፡፡

ስም---------------ክፍል------------ ተ.ቁጥር ------------መለያ ኮድ-------- እና ፆታ------

- ለትምህርት ቤታችሁ የመታወቅያ ወረቀት እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ጻፍ(ፊ)፡፡

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------

ይዘት ከ 25 ------------------------

አደረጃጀት ከ 20 -----------------------

ቃላት ከ25 -----------------------

የቋንቋ አተቃቀም ከ15 ---------------------

ስርዓተ ነጥብ ከ 15 --------------------

ድምር ከ 100 --------------------

# አባሪ 2

## ለዋናው ጥናት ለድህረ ትምህርት የቀረበ የጽሁፍ ፈተና

የዚህ የጽሁፍ ፈተና ዋና አላማ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት ተኮር የመጻፍ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽዖ መፈተሽ ነው፡፡የዚህን ጥናት አላማ ለማሳካት የሚቻለው እናንተ የምትጠየቁትን ጥያቄ በትክክል መመለስ ስትችሉ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የቀረበውን ጥያቄ በትክክል መልሱ፡፡የፈተናው ውጤትም በተመራማሪው ብቻ በሚስጢር ይያዛል፡፡ለምታደርጉት ትብብርም አጥኚው ልባዊ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ምድብ-------

ጊዜያዊ የመለያ ኮድ ቁጥር---------

ማሳሰብያ

ሀ.በመጻፊያ ወረቀቱ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ለ.የምትጽፈው (ፊ) ጊዜያዊ የመለያ ኮድ ቁጥሩን ብቻ ነው፡፡

የተማሪው ስም--------------------- ሴክሽን-------- ተ.ቁጥር-------- እና መለያ ኮድ-----ፆታ------

---

ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ለትምህርት ቤታችሁ የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ጻፍ (ፊ)፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

ይዘት ከ 25 -------------------

አደረጃጀት ከ 20 --------------------

ቃላት ከ 25 --------------------

የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 --------------------

ስርአተ ነጥብ ከ 15 ---------------------

ድምር ከ 100 ----------------------

## አባሪ 3

በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠየወቅ

ውድ ተማሪዎች፡-የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ ለአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ያላቸውን ተነሳሽነት ለመፈተሽ ነው፡ ፡መጠይቁ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የእናተን ዳራዊ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አማራጭ ጥያቄን የያዘ ነው፡፡ በውስጡም የተካተቱት የጥያቄዎች ብዛት ጥያቄዎች ናችው፡፡ ስለሆነም በዚህ መጠይቅ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ትክክለኛ ነው ብላችሁ የምታስቧቸውን ምላሾችበመምረጥ ለጥናቱ መሳካት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ ባክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ይህንን የጽሁፍ መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ በመሆናችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አጠቃላይ መመሪያ

- መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም
- በክፍል ሁለት የቀረቡትን መጠይቆች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ የመረጣችሁትን ምላሽ በያዘው ቁጥር የ ምልክት በማስቀመጥ ምላሻችሁን አመልክቱ፡፡

ክፍል አንድ ፡- ዳራዊ መረጃ

መመሪያ ፡-ከዚህ በታች ለተጠየቁት መረጃዎች ትክክለኛውን ምላሽ ክፍት በሆኑ ቦታዎች ላይ ሙሉ፡፡

ፆታ----------------እድሜ-------------ክፍል---------------------መ.ቁ--------------------

ክፍል ሁለት በአማርኛ ቋንቋ ለመጻፍ ክሂል ያላችሁን ተነሳሽነት በተመለከተ የቀረቡት ጥያቄዎመመሪያ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ከቀረቡት አማራጮች አንዱን መርጣችሁ በስሩ የ ምልክት በማስቀመጥ መልስ ስጡ፡፡

የክፍል ሁለት ምርጫዎች

በጣም እስማማለሁ

እስማማለሁ

መወሰን ያስቸግረኛል

ፈጽሞ አልስማማም

የተማሪው ስም-------------------- ሴክሽን-------- ተ.ቁጥር-------- እና መለያ ኮድ-----ፆታ------

ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ለትምህርት ቤታችሁ የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ጻፍ (ፊ)።

[illegible]

15/09/2016

[illegible]

| | | |
|---|---|---|
| ይዘት ከ 25 | 13 | 12 |
| አደረጃጀት ከ 20 | 14 | 15 |
| ቃላት ከ 25 | 10 | 12 |
| የቋንቋ አጠቃቀም ከ 15 | 10 | 10 |
| ስርአት ነጥብ ከ 15 | 9 | 8 |
| ድምር ከ 100 | 56 | 57 |

56.5

66

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግለ ግንዛቤ | | | | | | |
| 1 | በክፍል ውስጥ የሚሰጡኝ የመጻፍ ይዘት ቀላል እና ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 2 | በመጻፍ ትምህርት ጊዜ በየዕለቱ አዳዲስ ነገሮችን እማራለሁ፡፡ | | | | | |
| 3 | በክፍል ውስጥ የሚሰጡኝን የመጻፍ ይዘት በሚፈለገው መልኩ አከናውናለሁ፡፡ | | | | | |
| 4 | በመጻፍ ትምህርት ጊዜ ማከናወን የሚጠበቁብኝን ቅድመ ሁኔታዎች ጠንቅቄ ማወቄ ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል፡፡ | | | | | |
| 5 | በምጽፋቸው አጠቃላይ ጽሑፎች (አንቀጽ፣ ድርሰት፣...) ጥሩ ውጤት አግኝቻለሁ፡፡ | | | | | |

# አባሪ 4

**የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ውጤት**

| ቅድመ ፈተና ምድብ አንድ | | | | ድህረ ፈተና ምድብ አንድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮድ | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አማካይ | ኮድ | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አማካይ |
| B01 | 43 | 39 | 41.5 | B01 | 40 | 51 | 45.5 |
| B02 | 47 | 41 | 44 | B02 | 48 | 46 | 47 |
| B03 | 59 | 66 | 62.5 | B03 | 71 | 78 | 74.5 |
| B04 | 49 | 56 | 52.5 | B04 | 58 | 62 | 60 |
| B05 | 48 | 67 | 57.5 | B05 | 81 | 82 | 81.5 |
| B06 | 56 | 49 | 52.5 | B06 | 71 | 63 | 67 |
| B07 | 59 | 79 | 69 | B07 | 79 | 85 | 82 |
| B08 | 50 | 43 | 42.5 | B08 | 42 | 46 | 44 |
| B09 | 56 | 44 | 50 | B09 | 59 | 57 | 58 |
| B10 | 70 | 68 | 69 | B10 | 79 | 81 | 80 |
| B11 | 58 | 58 | 58 | B11 | 71 | 76 | 73.5 |
| B12 | 47 | 41 | 44 | B12 | 57 | 56 | 56.5 |
| B13 | 47 | 40 | 43.5 | B13 | 43 | 57 | 50 |
| B14 | 68 | 56 | 61 | B14 | 64 | 66 | 65 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| B15 | 61 | 63 | 62 | B15 | 82 | 80 | 81 |
| B16 | 81 | 76 | 78.5 | B16 | 83 | 81 | 82 |
| B17 | 46 | 40 | 43 | B17 | 47 | 44 | 45.5 |
| B18 | 71 | 69 | 70 | B18 | 90 | 83 | 86.5 |
| B19 | 60 | 53 | 56.5 | B19 | 67 | 62 | 64.5 |
| B20 | 47 | 41 | 44 | B20 | 45 | 39 | 42 |
| B21 | 50 | 49 | 49.5 | B21 | 61 | 68 | 64.5 |
| B22 | 54 | 59 | 56.5 | B22 | 44 | 39 | 41.5 |
| B23 | 41 | 35 | 38 | B23 | 45 | 40 | 42.5 |
| B24 | 54 | 47 | 50.5 | B24 | 45 | 49 | 47 |
| B25 | 49 | 46 | 47.5 | B25 | 45 | 45 | 45 |
| B26 | 57 | 58 | 57.5 | B26 | 49 | 57 | 53 |
| B27 | 53 | 49 | 51 | B27 | 46 | 40 | 43 |
| B28 | 48 | 45 | 46.5 | F31 | 41 | 59 | 50 |
| B29 | 46 | 44 | 45 | F32 | 42 | 62 | 52 |
| B30 | 41 | 37 | 39 | F33 | 51 | 51 | 51 |

# አባሪ 5

**የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ውጤት**

| ቅድመ ፈተና<br><br>ምድብ አንድ | | | | ድህረ ፈተና<br><br>ምድብ አንድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮድ | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አማካይ | ኮድ | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አማካይ |
| F01 | 50 | 45 | 47.5 | F01 | 41 | 36 | 48.5 |
| F02 | 86 | 85 | 85.5 | F02 | 66 | 80 | 73 |
| F03 | 52 | 48 | 50 | F03 | 44 | 48 | 46 |
| F04 | 57 | 50 | 53.5 | F04 | 48 | 54 | 51 |
| F05 | 48 | 48 | 48 | F05 | 45 | 48 | 46.5 |
| F06 | 47 | 47 | 47 | F06 | 47 | 53 | 50 |
| F07 | 56 | 57 | 56.5 | F07 | 54 | 59 | 57 |
| F08 | 56 | 56 | 56 | F08 | 50 | 68 | 59 |
| F09 | 59 | 65 | 64 | F09 | 57 | 71 | 64 |
| F10 | 50 | 47 | 48.5 | F10 | 45 | 55 | 50 |
| F11 | 51 | 48 | 49.5 | F11 | 45 | 56 | 51 |
| F12 | 50 | 48 | 49 | F12 | 43 | 59 | 51 |
| F13 | 64 | 53 | 58.5 | F13 | 47 | 73 | 60 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| F14 | 49 | 46 | 47.5 | F14 | 41 | 57 | 49 |
| F15 | 49 | 44 | 46.5 | F15 | 41 | 57 | 49 |
| F16 | 49 | 44 | 46.5 | F16 | 45 | 52 | 48.5 |
| F17 | 47 | 45 | 46 | F17 | 42 | 53 | 47.5 |
| F18 | 52 | 52 | 52 | F18 | 45 | 61 | 53 |
| F19 | 52 | 50 | 51 | F19 | 45 | 59 | 52 |
| F20 | 53 | 53 | 53 | F20 | 52 | 58 | 55 |
| F21 | 49 | 45 | 47 | F21 | 40 | 58 | 49 |
| F22 | 45 | 40 | 42.5 | F22 | 41 | 48 | 43.5 |
| F23 | 49 | 51 | 50 | F23 | 50 | 55 | 52.5 |
| F24 | 51 | 46 | 48.5 | E24 | 41 | 58 | 49.5 |
| F25 | 46 | 53 | 49.5 | F25 | 53 | 46 | 49.5 |
| F26 | 46 | 41 | 43.5 | F26 | 44 | 46 | 45 |
| F27 | 54 | 61 | 57.5 | F27 | 70 | 68 | 69 |
| F28 | 48 | 44 | 46 | F28 | 43 | 61 | 52 |
| F29 | 44 | 42 | 43 | F29 | 42 | 58 | 50 |
| F30 | 45 | 45 | 45 | F30 | 45 | 63 | 54 |